**የአስር ቀናት ጸሎት**

**የመሪዎች መምሪያ - የሶስቱ መላዕክት የጸሎት ጥሪ**

ወደ 2014 የ10 ቀናት የጸሎት ሳምንት እንኳን በደህና መጣችሁ፡፡ ጸሎት የተሐድሶ መወለጃ ስፍራ እንደሆነ እናምናለን፡፡ በጾምና በጸሎት በፈለግነው ጊዜ አምላካችን ብዙ ተዓምራትን ፈጽሞልናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ መለወጥን ሰጥቶናል፣ ለወንጌል ጉጉትን ፈጥሮልናል፣ ቤተክርስቲያናትን አነቃቅቷል፣ ግንኙነቶችንም ፈውሶልናል፡፡

የእግዚአብሔር ድምጽ ለመነቃቃት እየጠራችሁ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ለናንተ በሚሆን ተስፋ የተሞላ ነው፡፡ “በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።”2ዜና 7፡14

“እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፤ እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፥ የምስራች የሚሰበክላቸው ይገኛሉ።” ኢዩ 2፡32

” ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።” ያዕቆብ 4፡8

“እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።” ራዕይ 3፡20

አሁን በየትኛውም ስፍራ ብትሆኑ እግዚአብሔር ከምታስቡት በላይ በቅርባችሁ ነው፡፡ በቤተሰባችሁ ላይ፣ በምህበረሰቡ ላይና በአለም ላይ በረከትን ለማፍሰስ ይፈልጋል፡፡ በአሁኑ ሰኣት ለጸሎት እየቀረበ ባለው የሶስቱ መላዕክት ጥሪ አብራችሁን ተሳታፊ ሁኑ፡፡

ለአስሩ ቀናት የጸሎት ጊዜ የሚረዱ ጠቅለል ያሉ ነገሮች

**የየእለት የጸሎት መመሪያዎች**

ለአስሩ ቀናት የሚሆኑ የጸሎት መምሪያዎችን አዘጋጅተናል፡፡ እያንዳንዱ መመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ ለጸሎት የሚነበብ ጽሁፍ፣ ወደጸሎት የሚመሩ ጥቅሶች፣ የጸሎት ሐሳቦችና አብረው ቢዘመሩ ያልናቸውን መዝሙሮች አካተናል፡፡ የየእለቱን የጸሎት መመሪያ አባዝታችሁ እያንዳንዱ ተሳታፊ አብሮ እያነበበ እንዲከታተል መልካም እንደሆነ መጠቆም እንወዳለን፡፡

በአለም ዙሪያ ያሉ ቤተክርስቲያናት በየእለቱ የጸሎት ርእስ ላይ ባንድነት ይጸልያሉ፡፡ ጥቅሶቹን በመጠቀምና የጸሎት ጥያቄዎቹ ላይ በመጸለይ ከነርሱ ጋር ተባበሩ፡፡ በተሰጡት የጸሎት ርእሶች ሁሉ ላይ ለመጸለይ ሲባል መፍጠን ይገባል ብላችሁ አታስቡ፡፡ በትናንሽ ቡድኖች መከፋፈልና የጸሎት አደራዎችን አከፋፍሎ መጸለይ ትፈልጉ ይሆናል፡፡ መልካም ይሆናል፡፡

“የአለም አድቬንቲስት ቤተክርስቲያናት የጸሎት ጥያቄዎች” የሚል ጽሁፍንም አካተናል፡፡ በአለም ዙሪያ ለሚገኙ የአድቬንቲስት ቤተሰቦች መጸለይ አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን ቡድናችሁ ምናልባት ከአካባቢው ማህበረሰብ የጋበዛቸው ሰዎች ካሉ ለፍላጎቶቻችሁ ለመጸለይ ተጨማሪ ጊዜ መውሰድ ትችላላችሁ፡፡ እንግዶቻችሁን እንዴት አድርጋችሁ እንደምትቀበሉና የቡድኑ ክፍል መሆን እንዲችሉ እንደምታደርጉ ጌታ እንዲያሳያችሁ ጸልዩ፡፡

እያንዳንዱ የጸሎት ጊዜ የሚወስደው ሰዓት እንዲህ ቢሆን የሚል ጥቆማ

ቡድኑ በጸሎት ላይ ብቻ እንዲያተኩር የጸሎቱን ጊዜ ቀለል ያለ አድርጉት፡፡ በእያንዳንዱ ክፈል ላይ የምታሳልፉት የጸሎት ጊዜ ሊለያይ ይችላል፡፡ የሚኮተለውን መምሪያ እንደሐሳብ እንጠቁማለን፡፡

እንኳን ደህና መጣችሁና መግቢያ - 2-5 ደቂቃዎች

ከየእለት የጸሎት መምሪያ የሚነበብ ንባብን ማንበብ - 5 ደቂቃዎች

ከየእለት የጸሎት መምሪያ ላይ ከሚገኘው “የእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሱ መጸለይ” ከሚል የጥቅስ ክፍል እየጠቀሱ መጸለይ - 10-15 ደቂቃዎች

“ተጨማሪ የጸሎት ሐሳቦት/ጥቆማዎች/” ከሚለውና ከየእለት የጸሎት መምሪያ በተሰጡ ተጨማሪ ሐሳቦች ላይ መጸለይ - 20-30 ደቂቃዎች

የዝማሬና የምስጋና ጊዜ - 5-10 ደቂቃዎች

**ለሌሎች ጸልዩ**

እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር በልቡ ላስቀመጣቸው ከ5-7 ለሚጠጉ ሰዎች እንዲጸልይ አደፋፍሩ፡፡ የሚጸልዩላቸው ሰዎች ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ አብረዋቸው የሚሰሩ፣ ጎረቤቶቻቸው ወይም የሚያውቋቸው ሰዎች ሊሆን ይችላሉ፡፡ እነዚህን ስሞች በመምረጥና በነዚህ 10 የጸሎት ቀናት ወቅት ሰዎቹን በመድረስ ረገድ መንፈስ ቅዱስን እንዲጠይቁ አደፋፍሯቸው፡፡ የሚጸልዩላቸውን ሰዎች ስም የሚጽፉበትን ካርድ ወይም ወረቀት ልታድሏቸውም ትችላላችሁ፡፡

**በ10 ቀን ጸሎት የሰንበት ቀን አገልግሎ**

በሁለቱም ሰንበቶች በሚካሄድ መርሀ-ግብር ላይ የተለየ የጸሎት ትኩረትና የተመለሱ ጸሎቶችን ምስክርነቶች አካሂዱ፡፡ አዲስ መንገድ ተጠቀሙ፤ በየዕለቱ የጸሎት ስብሰባዎች ላይ እየተከሰቱ ያሉ ነገሮችን ለቤተክርስቲያን አባላት ለማሳወቅ የሚረዱ ብዙ መንገዶች ይኖራሉና፡፡

**የመጨረሻውን ሰንበትን የማክበሪያ መንገድ**

የመጨረሻው ሰንበት እግዚአብሔር በአስሩ ቀናት ጸሎት እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር በማስታወስ ታላቅ የደስታ ጊዜ እንዲሆን ሊታቀድ ይገባል፡፡ የተመለሱ ጸሎቶች ምስክርነት፣ በጸሎት ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት/ስብከት/ እና መዝሙሮችን አካትቱ፡፡ የየእለቱን ስብሰባዎች ያልተሳተፉ ሰዎች ከሌሎች ጋር የመጸለይን ደስታ መካፈል እንዲችሉ ጉባኤውን ወደጸሎት ጊዜ ምሩ፡፡ ለተጨማሪ ሐሳብ የሰንበት አምልኮ ሰዓት ነጥቦችን ተመልከቱ፡፡

**የአስር ቀናት ጸሎት ቀጣይነት**

በአስር ቀናት የጸሎት ጊዜ ውስጥ ማድረግ የጀመረውን ነገር እግዚአብሔር በቀጣይነት እንዲያደርገው ጸልዩ፡፡ ምናባትም በሳምንታዊ ጸሎት ልታስቀጥሉት ትችላላችሁ፡፡ ወይም ምናባት እግዚአብሔር በቀጣይነት ማህበሩን የመድረስ አገልግሎት እንድትጀምሩ ይፈልግ ይሆናል፡፡ ክፍት ሁኑና እግዚአብሔር የመራችሁን አድርጉ፡፡ ከርሱ ጋር በመጓዛችሁና የመራችሁን በማድረጋች እንደሚያስገርማችሁ እርግጠኛ ናችሁ፡፡ "ሌሎችን የመድረስ ተግዳሮት" የሚለው ጽሁፍ በተለያዩ የአገልግሎት ሐሳቦች የተሞላ ነው፡፡

ምስክርነቶች

እባካችሁ እግዚአብሔር በአስሩ የጸሎት ቀናት ውስጥ እንዴት ሲሰራ እንደነበር የምትመሰክሩ እና በሌላ አለም ላሉ የምታጋሩ ሁኑ፡፡ ታሪኮቹ ለብዙዎች ማደፋፈሪያ ይሆናሉ፡፡ ምስክርነቶች በሚከተለው ድህረ-ገጽ ሊላኩ ይችላሉ፡፡ www.tendaysofprayer.org.

**የተቀናጀ ጸሎት ጠቋሚዎች**

**ተስማሙ**

አንድ ሰው በአንድ ርዕስ ላይ በሚጸልይበት ጊዜ ሌሎች በመስማማት በተራቸው ጊዜ በርዕሱ ላይ ይጸልዩ፡፡ ይሄ ሐይል ያለው ነገር ነውና! አንድ ሰው በጸሎት ጥያቄው ላይ ስለጸለየ ሌላ ሰው መድገም የለበትም ብላችሁ አታስቡ፡፡ ማቴ 18፡19 በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርቡን እንዴት የሚያበረታታ ነገር ነው፡፡

**የእግዚአብሔርን ተስፋዎች መጠየቅ**

ቡድኑ በሚጸልይበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ተስፋ እንዲጠይቁ አደፋፍሯቸው፡፡ በችግሮቻችን ላይ ማተኮር ቀላል ነው፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ተስፋ እየጠቀስን ስንጸልይ እምነታችን ያድጋል፣ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለም ራሳችንን እናሳምናለን፡፡ የእግዚአብሔር ተስፋዎች አይኖቻችንን ከድካሞቻችንና ከችግሮቻችን ላይ አንስተን በኢየሱስ ላይ እንድናደርግ ይረዱናል፡፡ ለያንዳንዱ ድክመትና ትግል የመጽሐፍ ቅዱሱ ተስፋዎችን ማግኘትና ያንን እየጠቀስን መለመን እንችላለን፡፡ ደግሞም ሰዎች ተጨማሪ ተስፋዎችን ከቃሉ እንዲፈልጉና ጽፈው በማስቀመጥ ለወደፊት እየጠቀሱ መጸለይ እንዲችሉ አደፋፍሯቸው፡፡

**ጾም**

ከናንተ ጋር በ10 ቀናት ጸሎት የመሳተፋትን ሰዎች አንዳንድ አይነት ጾሞችን ማለትም ከቴሌቭዥን፣ ከፊልመም፣, ከበይነ-መረብ፣ ከጣፋጭ ነገሮች ወይም ከምግብ እንዲጾሙ ጋብዟቸው፡፡ ጉባኤው ይበልጥ ከክርስተስ ጋር እንዲያያዝ ጌታ እንዲረዳው ተጨማሪ ጊዜ ወስዳችሁ ጸልዩ፡፡ ቀለል ያለ ምግብን በመመገብ አዕምሯችን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ይበልጥ መቀበል እንዲችል እንፈቅዳለን፡፡

**መንፈስ ቅዱስ**

ስለአንድ ሰው ህይወት ወይም ስለአንድ ጉዳይ የምትጸልዩት ምን እንደሆነ እንደያሳያችሁ መንፈስ ቅዱስን መጠየቃችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ እኛ የምንለምነውን እንደማናውቅና መንፈስ ቅዱስ ግን ለኛ እንደሚቃትት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡

“በክርስቶስ ስም ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አመራርም ልንጸልይ ይገባል፡፡ ይህ የምንጸልየውን አናውቅም መንፈስ ቅዱስ ግን በማይነገር መቃተት ስለኛ ይለምናል (ሮሜ 8፡26) የሚለው ምን እንደሆነ ያሳየናል፡፡ እንዲህ አይነቱን ጸሎት በመመለስ እግዚአብሔር ይደሰታል፡፡ ጸሎታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጉጉትና ካለማቋረጥ በፊቱ ስናቀርብ፤ ከምጠይቀው በላይ አብልጦ ለመስጠት (ኤፌ 3፡20) ከእግዚአብሔር የተገባው ተስፋ በዚያ ውስጥ ይኖራል፡፡” (*Christ’s Object Lessons,* p. 147, emphasis supplied).

**የጸሎት ደብተር (ጸሎትና ምላሽ የሚመዘገብበት)**

በአስሩ የጸሎት ቀናት ውስጥ ተሳታፊዎች የየእለቱን የጸሎት ጭብጥ ወደውስጣቸው ማጥለቅ፣ ለእግዚአብሔር ራሳቸውን በሚገባ ለመስጠትና በረከቶቹን ለመገንዘብ እንዲችሉ የጸሎት ማስታወሻ መያዛችሁን ቀጥሉ፡፡ ጸሎቶቻንንና የእግዚአብሔርን ምላሽ እየጻፍን መቀጠላችን የማደፋፈሪያ መንገድ ነው፡፡

ከፈለጋችሁ በስብሰባው ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ምላሽ በግል የጸሎት ደብተራቸው ላይ እንዲመዘግቡ ጊዜ ልትሰጧቸው ትችላላችሁ፡፡ ወይም የቡድን የጸሎትና የጸሎት ምላሽ መመዝገቢያ ደብተር ሊኖራችሁ ይችላል፡፡ በደብተር፣ በትልቅ ወረቀት ወይም በኦንላይን ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ለጸሎታችን ምላሽ እንደሰጠ ዞር ብሎ ማየት የሚያስደስት ነው፡፡

**አክብሮት**

እግዚአብሔርን የማክበር አመለካከት እንዲኖር አደፋፍሩ፡፡ የምንቀርበው የአለማት ንጉስ በሆነው ዙፋን ፊት ነው፡፡ በአቀማመጥ፣ በአነጋገር ወይም በሁኔታችን ይህንን የጸሎት ጊዜ በግዴለሽነት አንመልከተው፡፡ ይህ ማለት ግን ሰው ሁሉ በያንዳንዱ የጸሎት ጊዜ መንበርከክ አለበት ማለት አይደለም፡፡ ሰዎች በጸሎቱ ጊዜ ለአንድ ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ ሲያሳልፉ ምቾት ሳይሰማቸው እንዳይቀሩ እንደተመቻቸው ሆነው እንዲጸልዩ (ቆመው፣ ተቀምጠው፣ ተንበርክከው፣ እግዚአብሔር እንደመራቸው) አድርጉ፡፡

**ረዥም ጸሎቶች**

ጸሎቶች አጭርና ግልጽ መሆን አለባቸው፡፡ ይሄ ሌሎችም ለመጸለይ እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ጸሎቶቻችሁ በአጫጭር አረፍተ ነገሮች እንዲወሰኑ አድርጉ፡፡ እያንዳንዱ ሰው በተደጋጋሚ ሊጸልይ ይችላል፡፡ አጫጭር የጸሎት አረፍተ ነገሮች የጸሎቱን ጊዜ አስደሳችና መንፈስ ቅዱስ ቡድኑ ውስጥ ያሉ ሰዎችን እንዴት እንደሚጸልዩ እንዲመራቸው ያደርጋል፡፡ እያንዳንዱን የጸሎት አረፍተ ነገር “ውድ አባት ሆይ” “ጌታ ሆይ” “`አሜን” እያለላችሁ መጀመርና መጨረስ አይኖርባችሁም፡፡ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር በቀጣይነት መነጋገር ነውና!

**የጸጥታ ጊዜ**

እንደመሪ የጸሎቱን ጊዜ ብቻችሁን አትቆጣጠሩት፡፡ ግባችን ሌሎችም እንዲጸልዩ ነውና፡፡ የጸጥታ ጊዜያት ደግሞ እግዘአብሔር ለልባችን እንዲናገር እድል ስለሚሰጡ ግሩም ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲሰራና እያንዳንዱ እንዲጸልይ ጊዜ ስጡ፡፡

*መዝሙር*

በጸሎት መሐል የሚዘመሩ የቡድን መዝሙሮች ለጸሎት ስብሰባው ውበት ይሰጡታል፡፡ ቢዘመሩ ተብለው ሐሳብ የሰጠንባቸው መዝሙሮች ከየጭብጥ ጽሁፉ መጨረሻ ላይ ተጠቅሰዋል፡፡ እነዚያን ሁሉ መዝሙሮች መዘመር እንዳለባችሁ አይሰማችሁ፡፡ እነዚህ ጥቆማ ብቻ ናቸው፡፡ መዝሙር ከአንድ ጸሎት ክፍል ወደ ሌላው መሸጋገሪያ ጥሩ መንገዶችም ናቸው፡፡

**የጸሎት አደራዎችን መቀበል**

ከሰዎች የጸሎት አደራዎችን አትቀበሉ፡፡ ከዚያ ይልቅ በነዚያ ጸሎቶች ላይ ራሳቸው እንዲጸልዩና ሌሎችም አብረዋቸው እንዲጸልዩ ንገሯቸው፡፡ ምክንያቱም ጊዜን ለመጠቀም! ከሰዎች የጸሎት አደራዎችን መቀበል ጊዜያችሁን ይወስዳል፡፡ በችግራችን ላይ ከመጸለይ ይልቅ ስለችግራችን እያወራን የጸሎቱን ጊዜ ስናጠፋው ሰይጣን ይደሰታል፡፡ ደግሞ የቡድን አባላት ብዙውን ጊዜ በተነገረው ችግር ላይ ምክርና የመፍትሄ ሐሳብ መስጠት ይጀምራሉ፡፡ ሐይል ከእግዚአብሔር ነው! ብዙ እንደጸለይን መጠን የርሱ ሐይል በብዛት ይለቀቅልናል፡፡

**የየእለት የግል ጊዜያችሁ**

ይህ በጣም አስፈላጊው ነው፡፡ እንደመሪ በግላችሁ በየእለቱ ከኢየሱስ እግር ስር ሆናችሁ ከርሱ ጋር በመነጋገርና ቃሉን በማንበብ ማሳለፋችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ እግዚአብሔር በህይወታችሁ የመጀመሪያ እንደሆነ እያሳወቃችሁት ከሆነ ለናንተ ግሩም የሆነ ልምምድ ይሆንላችኋል፡፡ "በታላቁ የተሐድሶ ጊዜ አለምን ያናወጠ ሐይል ከሚስጥር የጸሎት ስፍራ ወጥቶ ነበር፡፡ እዚያ በተቀደሰ መረጋጋት የጌታ አገልጋዮች በርሱ ተስፋዎች አለት ላይ እግሮቻቸው ቆመው ነበር፡፡" (*The Great Controversy*, p. 210) መሪ ሲጸልይ እግዚአብሔር በልቦች ላይ ይሰራል፡፡

## *መግቢያ*

ወደ 2014 የ10 ቀናት የጸሎት ጊዜ እንኳን በደህና መጣችሁ፡፡ ጸሎት የተሐድሶ መፈጠሪያ ስፍራ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ባለፉት ዘመናት በህብረት በፊቱ ቀርበን በጾምና በጸሎት በፈለግነው ጊዜ እግዚአብሔር ብዙ ተዓምራትን ሰርቷል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ብዙዎችን ወደራሱ መልሷል፣ ለወንጌል አገልግሎት አድሷል፣ ቤተክርስቲያናትን አነቃቅቷል፣ እንዲሁም ግንኙነቶችን ጠግኗል፡፡ ካለፉት አመታት የእግዚአብሔር ስራ ውስጥ ጥቂቶች ምስክርነቶች እነሆ፡

የአስር ቀናት ጸሎት ሕይወቴን በእርግጥ ለውጧል፤ ለኔ አስገራሚ የመመለሻ ጊዜ ነበር፡፡ (Ruth K.)

"በትምህርቶቹ በጣም ልባችን ሲነካ ነበር፤ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ልቦቻቸውን ሲያነሱ ነበር፤ በእግዚአብሔር ተስፋዎች ላይ ተመስርቶ መጸለይና የኢየሱስን ድንቅ ስጦታ (መንፈስ ቅዱስን) መጠየቅ ምን እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ተምረን ነበር"

**(Moureen K.)**

“ከአስር ቀናት ጸሎት በፊት በቤተክርስቲያኔ ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች ታመው ነበር፤ ነገር ግን በጸሎቱ ጊዜ መካከለኛ ቀናት ተፈወሱ፤ በተጨማሪ 7 ሰዎች ህይወታቸውን ለጌታ ሰጥተው ተጠመቁ፡፡” **(Mugabe G.)**

የእግዚአብሔር ድምጽ ለመነቃቃት ሲጠራችሁ ነበርን? መጽሐፍ ቅዱስ ለናንተ በሚሆኑ ተስፋዎች የተሞላ ነው፡፡

“በስሜ የተጠሩት ህዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፤ ፊቴንም ቢፈልጉ፤ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፣ እኔም ከሰማይ ሆኜ እሰማለሁ ሐጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ” 2ዜና 7፡14

“እናንተም ትሹኛላችሁ፤ በፍጹም ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ” ኤር 29፡13

“የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል” ኢዩ 2፡32

“ወደ እግዚብሔር ቅረቡ እርሱም ወደእናንተ ይቀርባል” ያዕ 4፡8

“`እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምጼን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደርሱ እገባለሁ፤ ከርሱም ጋር እራት እበላለሁ” ራዕይ 3፡20)

በአሁኑ ሰዓት በየትም ቦታ ብትሆኑ እግዚአብሔር ከምታስቡት በላይ ቅርባችሁ ነው፡፡ በቤተሰባችሁ፣ በቤተክርስቲያችሁ፣ በማህበረሰባችሁና በአለማችሁ ላይ በረከቶቹን ለማፍሰስ ይፈልጋል፡፡

**የጸሎታችን ጭብጥ - የሶሰቱ መላዕክት መልዕክት የጸሎት ጥሪ**

በዚህ አመት በአስሩ የጸሎት ቀናት ወቅት በመንፈስ ቅዱስ ሐይል አማካኝነት መነቃቃትና ተሐድሶን እንድትፈልጉ እንጋብዛችኋለን፡፡ በሶስቱ መላዕክት መልዕክት እየተመራችሁ ስትጸልዩ በአዲስ ሁኔታ ያብሩላችሁ፤ በተጨማሪም እናንተንና ቡድናችሁን ከየሱስ ጋር ወደሚሆን የጠለቀ ግንኙነት ይምሯችሁ፡፡

እግዚአብሔር በእኛ ህይወትና በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ዛሬ አስገራሚስራዎችን መስራት ይፈልጋል፡፡ የርሱ እቅድ ከችሎታችን ያለፈ ሲሆን ያዘጋጀውን ስራ ማከናወን የምንችለው በማያቋርጥ ጸሎት ከርሱ ጋር በመገናኘት ብቻ ነው፡፡ “ጥራኝ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ሐይለኛ ነገር አሳይሃሁ” ኤር 33፡3 ይለናል፡፡

ለተሐድሶ፣ ለመጨረሻ ዘመን ጥሪያችን ለሚያበቃ አዲስ ህይወትና ተስፋ ለተገባው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ከኛ ጋር በጸሎት ተባበሩ፡፡

**ለጸሎት ጊዜያት የሚረዱ ጠቃሚ መመሪያዎች**

- ጸሎቶቻችሁን አጠር አድርጓቸው - በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ አንድ ወይም ሁለት አረፍተ ነገር ብቻ! ልክ ወሬ እንደምታወሩ በጸሎት ጊዜ እንደምትፈልጉት በዛ አድረጋችሁ መጸለይ ትችላላችሁ፡፡
- ዝመታን አትፍሩ - ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን ለመስማት እንዲችሉ ለሁሉ እድል ይሰጣልና

- መንፈስ ቅዱስ እንደመራን መጠን መዝሙሮችን ቢጋራ መዘመርም ታላቅ በረከት ነው። ለዚህ ጊዜ የሙዚቃ መሳሪያ አያስፈልጋችሁም። ያለ ሙዚቃ መዘመር ይመረጣል።
- የጸሎት ርዕሶችን ከመለዋወጥ ይልቅ እንዲሁ በቀላሉ ራሳችሁ ጸልዩባቸው። ከዚያም ሌሎች የናንተን ጸሎት ሰምተው ስለርሱ ይጸልያሉ፤ የሚያስፈልጋችሁንም የተስፋ ቃል ያነሳሉ።

የተስፋ ቃሎችን ጠቅሶ መለመን

በጸሎቶቻችን ውሰጥ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋዎች ጠቅሶ መለመን ለኛ ትልቅ እድል ነው። የርሱ ትዕዛዛትና ምክሮች ሁሉ ተስፋዎችም ጭምር ናቸው። በርሱ ሐይል የማይከናወን ነገርን  እኛን ፈጽሞ አይጠይቀንም።

በፍላጎቶቻችን፣ በችግሮቻችንና በተግዳሮቶቻችን ላይ ማተኮርና በጸሎታችን ጊዜ ስለነርሱ ማቀስና ማዘን ቀላል ነው።። የጸሎት አላማው ግን ይህ አይደለም። ጸሎት እምነታችንን የሚያጠናክር እንዲሆን ነው። በጸሎት ጊዜ የአምላክን ተስፋዎች እንድንጠይቅ የምናደፋፍራችሁ ለዚህ ነው ። ዓይኖቻችሁን ከራሳችሁና ከድካማችሁ ላይ አንሱና ወደ ኢየሱስ ተመልከቱ። ወደርሱ በመመልከት ወደርሱ ምስል እንለወጣለን።

ኤለን ኋይት ይህን ማደፋፈሪያ ትሰጣለች "በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለው ተስፋ ሁሉ ለኛ ነው። በጸሎታቻችሁ የያህዌን የተስፋ ቃል አቅርቡና በእምነት ተስፋዎቹን ጠይቁ። በእምነት ብትጠይቁ መንፈሳዊ በረከቶችን እንደምትቀበሉ ቃሉ ማረጋገጫ ነው። መጠየቃችሁን ቀጥሉ፤ ከምታስቡት በላይ በተትረፈረፈ ሁኔታ ትቀበላላችሁ።" (*In Heavenly Places*, p. 71).

የርሱን ተስፋዎች መጠየቅ የምትችሉት እንዴት ነው? ስለሰላም ስትጠይቁ ዮሐ 14፡27ን ጠቅሳችሁ "ጌታ ሆይ በቃልህ ውስጥ ሰላሜን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም አለም እንደሚሰጥ አይደለም፤ ልባችሁ አይታወክ አይፍራም" ብለኸናልና ከኛ ጋር እንዲኖር እሰጣችኋለሁ ያልከንን ሰላም ስጠን" ብላችሁ ጠይቁ። ምንም እንኳን ወዲያውኑ ባይሰማችሁ ጌታ ግን ሰላሙን እንደሰጣችሁ በማመን አመስግኑ።

**ጾም**

በነዚህ 10 ቀናት የዳንኤልን ጾም እንድትጾሙ እናደፋፍራለን። አመቱን በጸሎትና በጾም መጀመር በምንቀበለው አመት ውስጥ ህይወታችንን ለጌታ ቀድሰን እንድንሰጥ የሚያስችል ድንቅ መንገድ ነው። ኤለን ኋይት እንዲህ ትነግረናለች "ከአሁን ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የእግዚአብሔር ሰዎች ይበልጥ ቅን፣ ይበልጥ የነቁ፣ በመሪያቸው ጥበብ እንጂ በራሳቸው ጥበብ የማይታመኑ ሊሆኑ ይገባል። ለጾምና ጸሎት ጊዜን ሊቀድሱ ይገባል። ምናልባት ከምግብ ሙሉ ለሙሉ መራቅ ላያስፈልግ ይችል ይሆናል። ነገር ግን ቀለል ያለ ምግብ እየተመገቡ ሊጸልዩ ይችላሉ።" (*Counsels on Diet and Foods*, pp. 188, 189).

ለአስር ቀናት ያህል ፍራፍሬና አትክልትን ይመገብ እንደነበር ስለዳንኤል እናውቃለን። በነዚህ 10 ቀናት እጅግ ቀላል የሆኑ ምግቦችን እንድትጠቀሙ እናደፋፍራለን። የእግዚአብሔርን ድምጽ በግልጽ መስማትና ይበልጥ ወደርሱ መቅረብ ከፈለግን የምንመገበው ምግብ እንቅፋተ እንዳይሆንብን እርግጠኞች ልንሆን ይገባል።

ጾም ከምግብ የመከልከል ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ከቴሌቭዥን፣ ከፊልም፣ ከኮምፒዩተር ጌሞችና ከፌስቡክም ሆነ ከዩቱብ እንድትጾሙ እናደፋፍራለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ በራሳቸው መጥፎ ያልሆኑ ነገሮች ጊዜያችንን ሊወስዱብን ይችላሉ፡፡ ከጌታ ጋር ይበልጥ ጊዜ መውሰድ እንድትችሉ ይህንን ጊዜ የሚሻሙባችሁን ነገሮች በተቻለ መጠን ወደ ጎን አድርጓቸው፡፡

ጾም መጾም ከእግዚአብሔር ዘንድ ተዓምራትን የማግኛ ፈጣን መንገድ አይደለም፡፡ ይልቁንም እግዚአብሔር በኛ ውስጥና በኛ ይሰራ ዘንድ ራሳችንን ማዋረድ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ

ስለአንድ ሰው ህይወት ወይም ስለአንድ ጉዳይ የምትጸልዩት ምን እንደሆነ እንደያሳያችሁ መንፈስ ቅዱስን መጠየቃችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ እኛ የምንለምነውን እንደማናውቅና መንፈስ ቅዱስ ግን ለኛ እንደሚቃትት መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡

“በክርስቶስ ስም ብቻ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አመራርም ልንጸልይ ይገባል፡፡ ይህ የምንጸልየውን አናውቅም መንፈስ ቅዱስ ግን በማይነገር መቃተት ስለኛ ይለምናል (ሮሜ 8፡26) የሚለው ምን እንደሆነ ያሳየናል፡፡ እንዲህ አይነቱን ጸሎት በመመለስ እግዚአብሔር ይደሰታል፡፡ ጸሎታችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በጉጉትና ካለማቋረጥ በፊቱ ስናቀርብ፤ ከምጠይቀው በላይ አብልጦ ለመስጠት (ኤፌ 3፡20) ከእግዚአብሔር የተገባው ተስፋ በዚያ ውስጥ ይኖራል፡፡” (*Christ’s Object Lessons,* p. 147, emphasis supplied).

እምነት

“ጸሎትና እምነት በምድር ላይ ያለ የትኛውም ሐይል ሊያደረገው የማይችለውን ነገር ያከናውናል”(*The Ministry of Healing*, p. 509). በማለት የትንቢት መንፈስ ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም “ለያንዳንዱ ተስፋ የተገባልን ስጦታ መጠየቅ፣ እንደምንቀበል ማመንና ለተቀበልነው በምላሹ ጌታን ማመስገን” (*Education*, p. 258) እንዳለብን ይነግረናል፡፡ ስለሆነም ጌታ ሊያደርግ ስላለው ነገር ገና ሳይፈጸም አስቀድመን በእምነት የማመስገንን ልምድ ይኑረን፡፡

**ለሌሎች ጸልዩ**

በነዚህ አስር ቀናት ውስጥ አግዚአብሔር በህይወታችሁ ውስጥ ላስቀመጣቸው ሰዎች በተከታታይ እንድትጸልዩ እናደፋፍራለን፡፡

ከ5-7 ለሚጠጉ ሰዎች እንዲጸልይ አደፋፍሩ፡፡ የሚጸልዩላቸው ሰዎች ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ አብረዋቸው የሚሰሩ፣ ጎረቤቶቻቸው ወይም የሚያውቋቸው ሰዎች ሊሆን ይችላሉ፡፡ እንድትጸልዩለት የሚፈልግ ሰው ካለም ለርሱ ለመጸለይ ጊዜ ውሰዱ፡፡ ስሞቹን ጻፉና በደህና ቦታ አስቀምጡ፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ፡፡ እግዚአብሔር ለጸሎታችሁ በሚሰጠው መልስ ትደነቃላችሁ፡፡

**በአስሩ ቀናት የጸሎት ጊዜ ወጥቶ ሌሎችን ማገልገል**

እንድንጸልይ ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ፍላጎት እንድናገለግልም ኢየሱስ ይጠራናል፡፡ “ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና” ማቴ 25፡35-36

የፈውስ አገልግሎት በሚለው መጽሐፍ እንዲህ እናነባለን “ሁለት ነገሮችን ያማከለ ህይወት ልንኖር ይገባል፡- የማሰብና የመተግበር ህይወት፤ የጽሞና ጸሎትና የቅንነት ስራን” *The Ministry of Healing,* 512 ከአዳኛችን እጅግ የበዛ ፍቅርን ተቀብለናል፤ ያንን ፍቅር ለወዳጆቻችን፣ ለጎረቤቶቻችንና ለማናውቃቸው የተቸገሩ ሰዎች ሁሉu የማጋራት እድሉም አለን፡:

ከአስር ቀናት ጸሎት በኋላ እናንተና ቤተክርስቲያናችሁ ሌሎችን እንዴት ማገልገል እንደምትችሉ ራሳችሁን ጠይቁ፡፡ ታድያ ያንን ለማድረግ ስትንቀሳቀሱ ከጸሎት እንዳያስተጓጉላችሁ አትፍቀዱ፡፡ “ሌሎችን ለማገልገል የምናደርገው ጥረት በብዙ ሚስጥራዊ ጸሎት ሊደገፍ ይገባል፡፡ ሰዎችን የማዳን ሳይንስ ታላቅ ጥበብ የሚጠይቅ ነገር ነውና፡፡ ከሰዎች ጋር ከመገናኘታችሁ በፊት ከክርስቶስ ጋር ተገናኙ፡፡ በሰማያዊ ጸጋ ዙፋን ስር ሰዎችን ለማገልገል ዝግጅታችሁን አድርጉ” (*Prayer*, p. 313).

በ10 ቀን ጸሎት ድህረ ገጽ ላይ ሌሎችን ለመድረስ የሚረዱ ብዙ ሐሳቦችን ታገኛላችሁ፡፡ በፍላጎት በተሞላው አለም ውስጥ እጆቹና እግሮቹ እንድትሆኑለት ኢየሱስ ይጋብዛችኋል፡፡

ለየዕለት ጸሎት መምሪያ ጽሁፍ ዋናውን አበርክቶት ያደረጉት ዶክተር ማርክ ፊኒሊ ናቸው፡፡

ጽሁፉ የተዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤ/ክ ዋና መስሪያ ቤት የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡

**ስለ ጽሁፉ እቅራቢ**

ዶክተር ማርክ ፊኒሊ ቀድሞ የ “Is Written” ተናጋሪና መሪ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩና የጀነራል ኮንፍራንስ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው እያገለገሉ ሳሉ ጡረታ የወጡ ናቸው፡፡ አሁንም ቢሆን በፈቃድ በማገልገል ላይ ያሉ ወንጌላዊ ሲሆን ከ150 በላይ ተከታታይ የወንጌል ስብከቶችን በ80 ሐገሮች ያቀረቡ እንዲሁም በአለም ዙሪያ በ17 የሚጠጉ ማሰራጫዎች እያስተማሩ ያሉ ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቶች፣ የወንጌል ተቋማትና በሚጋበዙባቸው ስብሰባዎች ላይ መልዕክቶችን በቋሚነት እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ከ70 በላይ መጽሐፎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን፣ አጫጭር ጽሁፎችና የወንጌል አገልግሎት ማካሔጃ ጽሁፎችን ጨምሮ የተለያዩ መንፈሳዊ ጽሁፎችን የጻፉ ናቸው፡፡ ሶስት ልጆች አሏቸው፡፡ ዛሬ እሳቸውና ባለቤታቸው ወይዘሮ ቴኒዬ በሃይማርክት ቨርጂኒያ ውስጥ በሚገኘው ህያው ተስፋ የወንጌል አገልግሎት ስልጠና ማእከል ውስጥ እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

ተጨማሪ ጽሁፎች

በሶስቱ መላዕክት መልዕክት ርዕስ ላይ ተጨማሪ ጽሁፎችን ለማግኘት የሚከተለውን ድህረገጽ ተመልከቱ፡፡
www.threeangels.info

**የሌሊት ጸሎት**

የሌሊት ጸሎት ማካሄድ የአስር ቀናት ጸሎት ክፍል እንደሆነ አድርጋችሁ ቁጠሩ፡፡ ለምሳሌ ከምሽቱ 12 ጀምራችሁ ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ መጨረስ! ለቡድናችሁ አመቺ የሆነውን ሰዓት መምረጥ ትችላላችሁ፡፡

**የሌሊት ጸሎት ለምን አስፈለገ**

ሳያንቀላፉ ሌሊቱን ሁሉ በመጸለይ ምንም የተለየ ቅዱስ ነገር የለበትም፡፡ ሆኖም ግን ምሽት ሰዎች በተግባር የማይወጠሩበትና የማይጣደፉበት ብቸና ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ አላማችሁ ሌሊቱን ሁሉ ንቁ መሆን ብቻ ሳይሆን እንደአስፈላጊነቱና እግዚአብሔር እንድትጸልዩበት የሚፈልጋቸው ብላችሁ የሚሰማችሁ ነገሮች ሁሉ ላይ ለመጸለይ ነው፡፡

ብዙ ሰዎች የሌሊቱን ጸሎት እንዲመሩት ሐሳብ እንሰጣለን፡፡ በመሃከል የተወሰኑ የእረፍት ጊዜያት ይኑሩ፡፡ እንደመሪ ምን ጊዜ ላይ እረፍት ማድረግ እንዳለባችሁ የተሳታፊዎችን ሁኔታ እያያችሁ መሆን አለበት፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችንም የምታነቡበትን ጊዜ ማካተት ትችላላችሁ፡፡ ለቡድናችሁ ይሻላል ብላችሁ በምታስቡት ላይ በመመርኮዝ ሐሳብ የተሰጠባቸውን ነገሮች ሁሉ ማካተት ወይም የተወሰኑትን ማካተት ትችላላችሁ፡፡ ቅደም ተከተሉን መቀየር ካለባችሁም ነጻነት ይሰማችሁ፡፡

ለሌሊት ጸሎት የሚያግዝ ቅደም ተከተል

**በምስጋና የጸሎት ጊዜ ጀምሩ፡፡** በጸሎቶቻችሁና በዝማሬዎች አምላክን አመስግኑ

**ሐጢአትን ለመናዘዝ ጊዜ ውሰዱ፡፡** እግዚአብሔር ጸሎታችሁን እንዳይሰማ የሚከለክል ነገር እንዳይኖር እርግጠኞች ሁኑ፡፡ ለሰዎች የግል የንስሐ ጊዜ ስጡ፡፡ የጋራ የንስሐም ጊዜ ይኑራችሁ፡፡ ሰዎች የግል ሐጢአቶቻቸውን እንዲናዘዙ አደፋፍሯቸው፡፡ በህዝብ መካከል የሚናዘዙት ሰዎች የሚያውቋቸውን ሐጢአቶች ብቻ ይሁን፡፡ በዳን 9፡1-9 ስለህዝቡ ሲጸልይና በግልጽ ስለህዝቡ ሐጢአት ሲናዘዝ እናነባለን፡፡

በጸሎት ስብሰባው ላይ ስለተገኙት ሰዎች ፍላጎቶች ጸልዩ፡፡ ብዙ ሰዎች የተጎዱና እንዲጸለይላቸው የሚፈልጉ ይሆናሉ፤ ወይም በጣም ጸሎት የሚያስፈልገው ሰው ሊኖር ስለሚችል ለይታችሁ እወቁና ጸልዩለት፡፡ ክብ ስሩና በመካከል ጠረጴዛ አስቀምጡ፤ የጸሎት ጥያቄ ያላቸው ወደ ጠረጴዛው መጥተው የጸሎት አደራ እንዲሰጡ ጋብዟቸው፡፡ ከዚያም የጸሎት ጥያቄ ባቀረበው ሰው ዙሪያ ተንበርክካችሁ የእግዚአብሔርን ተስፋ በመጥቀስ ስለ ጸሎት አደራው ጸልዩ፡፡

ሁለት ሁለት ሆኖ መጸለይ፡፡ እህቶች በአንድ ክፍል ወይም ስፍራ በአንዲት እህት መሪነት እንዲጸልዩ አድርጉ ወንዶች ደግሞ በሌላ ክፍል ወይም ስፍራ፡፡ ብዙ የግል ጉዳዮች ለሁሉ የማይነገሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከተመሳሳይ ጾታ ጋር ተጋርቶ ለመጸለይ የሚቀሉ ሊሆኑ ይችላሉና ነው፡፡

ከተከፋፈላችሁበት ስትመለሱ በህብረት ሆናችሁ ስለቤተክርስቲያንና ስለማህበረሰቡ ጸልዩ፡፡ ለአለም ቤተክርስቲያን የጸሎት ጥያቄዎች ለመጸለይም ጊዜ ውሰዱ፡፡ (እነዚህ በአስር ቀን የጸሎት ጽሁፍ ውስጥ በተለይ ተዘርዝረው የሚገኙ ናቸው)፡፡ በፍጥነት ሁሉንም ርዕስ መነካካት እንዳለባችሁ አይሰማችሁ፡፡ ምናልባትም በትናንሽ ቡድን ተከፋፍላችሁ የተወሰኑ የጸሎት ርዕሶችን በመያዝ መጸለይ ትፈልጉ ይሆናል፡፡ መልካም ነው፡፡

**በስም ለተጠቀሱ ሰዎች መጸለይ፡፡** በነዚህ አስር የጸሎት ቀናት ውስጥ እየጸለያችሁላቸው ላሉ 5 ወይም 7 ሰዎች ጸልዩ፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምረጡና በርሱ ላይ ጸልዩ**

**በሌላ የምስጋና ጸሎት ያንን የጸሎት ክፍለ ጊዜ ደምድሙ፡፡**

## ለአስር ቀናት ጸሎት ሌሎችን የመድረስ ግድድሮሽ

ኢየሱስ ክርስቶስ እንድንጸልይ ብቻ ሳይሆን በዙሪያችን ያሉትን ሰዎች አካላዊና መንፈሳዊ ፍላጎት እንድናገለግል ይጠራናል፡፡ ማቴ 25፡35-36

የፈውስ አገልግሎት በሚለው መጽሐፍ እንዲህ የሚል እናነባለን፡፡ “ሁለት ነገሮች ላይ ያተኮረ ህይወት ሊኖረን ይገባል፤ የማሰብና የመተግበር ህይወት! የጸጥታ ጸሎትና በትጋት የመስራት፡፡” (p. 512). ከአዳኛችን ብዙ ፍቅርን ተቀብለናል በመሆኑ ያንን ፍቅር ከወዳጆቻችን፣ ከጎረቤቶቻችንና ከሚፈልጉ እንግዶች ጋር የመጋራት እድሉ አለን፡፡

ከአስሩ የጸሎት ቀናት በኋላ እንዴት አድርጋችሁ ሌሎችን ማገልገል እንደምትችሉ እግዚአብሔርን ጠይቁት፡፡ እነዚህን የማገልገል እንቅስቃሴዎች ስታደራጁ ሳለ ከመጸለይ እንዳትስተጓጎሉ ተጠንቀቁ፡፡

ከአስር ቀናት ጸሎት በኋላ እናንተና ቤተክርስቲያናችሁ ሌሎችን እንዴት ማገልገል እንደምትችሉ ራሳችሁን ጠይቁ፡፡ ታድያ ያንን ለማድረግ ስትንቀሳቀሱ ከጸሎት እንዳያስተጓጉላችሁ አትፍቀዱ፡፡ “ሌሎችን ለማገልገል የምናደርገው ጥረት በብዙ ሚስጥራዊ ጸሎት ሊደገፍ ይገባል፡፡ ሰዎችን የማዳን ሳይንስ ታላቅ ጥበብ የሚጠይቅ ነገር ነውና፡፡ ከሰዎች ጋር ከመገናኘታችሁ በፊት ከክርስቶስ ጋር ተገናኙ፡፡ በሰማያዊ ጸጋ ዙፋን ስር ሰዎችን ለማገልገል ዝግጅታችሁን አድርጉ” (*Prayer*, p. 313).

ሌሎችን ልታገለግሉ የምትችሉባቸው አንዳንድ መንገዶችን ከታች ለመዘርዘር ሞክረናል፡፡ ለማህበረሰባችሁ ገጣሚ የሚሆነውን ምረጡ፡፡ የራሳችሁንም ሐሳብ ለማካተት ነጻነት ይሰማችሁ፡፡

- ታሞ ተኝቶ ላለ ሰው ምግብ ሰርቶ መውሰድ
- ወደ ማህበራዊ ስብሰባችሁ ጎረቤትን ወይም አብረዋችሁ የሚሰሩትን መጋበዝ
- ቤት አልባ ለሆነ ሰው ወይም ለጎዳና ተዳዳሪ ምግብ መስጠት
- ልብስ የሚያስፈልገው ካለ ልብስ መስጠት
- ሽማግሌን ወይም አሮጊትን በቋሚነት በምግብ፣ በቤት ስራ፣ የምግብ እቃዎችን በመግዛት.. ማገዝ
- ዳቦ ጋግራችሁ ምግብ ላጠረው ጎረቤታችሁ መውሰድ
- ጎረቤቶቻችሁ በሚንቀሳቀስበት ፕሮጀክት ማገዝ
- አካል ጉዳተኞችን የሚያገለግሉትን ለማሳረፍ ከጉዳተኛው ጋር መቆየትና ማገልገል
- አዲስ ጎረቤቶች ካሏችሁ መተዋወቅና እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት ምግብ መጋበዝ ወይም አዘጋጅቶ ወደ ቤታቸው መሄድ
- ለተቸገሩ ሰዎች የሚያግዟቸውን ነገር ገዝቶ ይዞ መሄድ
- የማትጠቀሙበት መነጽር ካለ በእድሜ ለገፉ ሰዎች መስጠት
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚፈልጉ ጎረቤቶች ካሉ መስጠት
- የህጻናት ማሳደጊያና የአዛውንት መጦሪያ ቦታዎችን መጎብኘትና መደገፍ
- ለተቸገረ ተማሪ ገንዘብ፣ ደብተር ወይም ምግብ መስጠት
- ልብስ አሰባስባችሁ ከአካባቢያችሁ ጀምራችሁ ለሚያስፈልጋቸው ማደል
- የማትጠቀሙበት ላፕቶፕ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ እቃ ካለ ለሚያስፈልጋቸው መስጠት
- የጤና ኤክስፖን ማቀናጀት
- ለእስረኞች ካርድ ወይም ሌላ ነገር መላክ
- የወንጌል ጥረት ማቀናጀት
- ጎረቤቶቻችንን ወደ ቤታችን መጋበዝና መጫወት
- ይወዱታል ብላችሁ የምታስቡትን መጽሐፍ መስጠት
- ትራክቶችን መስጠት
- አንድ ሰው ክርስቶስን እንዲቀበል መጋበዝ
- አቅም ካለ የምግብ ማብሰል ማሰልጠና ትምህርት ቤት ከፍቶ በነጻ ማሰልጠን
- የሚወዱትን በሞት ያጡ ካሉ ለማጽናናት መሄድ
- በሆስፒታል የተኛ ሰው ካለ ለመርዳት ወይም በሆነ መንገድ ለማደፋፈር መጎብኘት
- በእድሜ ለገፉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ወይም ሌላ ታሪክ ማንበብ
- የልብስ ስፌት ቡድን መጀመርና ልብስ እየሰፉ ለሚያስፈልጋቸው መስጠት

- ማየት ወይም መስማት ለተሳነው ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ
- በቤታችሁ የወጣቶች ምሽት ማዘጋጀትና መጋበዝ
- ጥቃት የደረሰባቸውን የሚያግዙ ማገገቢያ ስፍራዎችን በፈቃደኝነት ማገልገል
- ለህጻናት ማሳደጊያዎች መጻህፍትን ማበርከት
- የቤተክርስቲያን ልጆችን ይዞ ወደ ህጻናት ማሳደጊያ ወይም ወደ አዛውንቶች መጦሪያ ሄዶ መንብኘትና ማገዝ
- የጽዳት ቀን አቅዶ አካባቢን የማጽዳት ስራ መስራት
- በቤተክርስቲያናችሁ ውስጥ የጤናማ አኗኗር ዘይቤ ክለብ መጀመርና ወዳጆችንና ጎረቤቶችን መጋበዝ
- መንፈሳዊ መልዕክት ያለው ቪዲዮ አብሯችሁ መመልከት የሚፈልጉ ካሉ መጋበዝ፡፡ አብራችሁ እያያችሁ ሳለ መንፈስ ቅዱስ ልባቸውን እንዲነካ መጸለይ፡፡
- የራሳችሁን ሌሎች ፕሮጀክቶችን ማቀድ

በምስክረነት ላይ ተጨማሪ ጽሁፎችን ለማግኘት የሚከተለውን ድህረ ገጽ ጎብኙ፡፡

www.revivalandreformation.org/resources/witnessing.

**በጸሎት ውስጥ የምንጠቅሳቸውና የምንጠይቅባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎች**

ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጡ ተስፋዎች

“በኋለኛው ዝናብ ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዝናቡን ለምኑ፤ እግዚአብሔር መብረቅ ያደርጋል፤ እርሱም የበልግ ዝናብን ለእያንዳንዱም በሜዳ ውስጥ ሣርን ይሰጣል።”ዘካ 10፡1

“እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?” ሉቃስ 11፡13

“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል። እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤” ዮሐ 14፡26፤ 16፡8

“እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።”ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።ዮሐ 14፡12-14

“መልሶም፡- ለዘሩባቤል የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡” ዘካ 4፡6

<u>እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚመልስ የተሰጡ ተስፋዎች</u>

“በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።” ዮሐ 15፡7

“እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።” ዕብራ 4፡16

“ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።” ማርቆስ 11፡24

“በመከራ ቀን ጥራኝ፥ አድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ።” መዝ 50፡15

“ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።” ማቴ 18፡19

“አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው።” ማቴ 21፡22

“እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።” ዮሐ 14፡13፣14

“በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።” ዮሐ 16፡23፣24

“በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል።የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።” 1ዮሐ 5፡14፣15

<u>የእግዚአብሔርን ሐይል ስለማግኘት የተሰጠ ተስፋ</u>

“በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ፤ ሣራም ልጅን ታገኛለች።” ዘፍ 18፡14

“እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፥ እናንተም ዝም ትላላችሁ አላቸው።” ዘጸ 14፡14

“ኢየሱስም ተመለከታቸውና፦ ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላልና አለ።” ማር 10፡27

“የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።” 1ተሰሎ 5፡24

“ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ፥ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።” ዕዮብ 42፡2

“እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን? እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?” ሮሜ 8፡31፣32

“ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን?” ዘሁ 23፡19

"ያዕቆብ ሆይ፥ እስራኤልም ሆይ፡- መንገዴ ከእግዚአብሔር ተሰውራለች ፍርዴም ከአምላኬ አልፋለች ለምን ትላለህ? ለምንስ እንዲህ ትናገራለህ?አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም።ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፥ ጕልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል።ብላቴኖች ይደክማሉ ይታክቱማል፥ ጕበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤
እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፥ አይደክሙም።" ኢሳ 40፡28-31

<u>እግዚአብሔር እንደሚመራን የተሰጠን ተስፋ</u>

"በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?" ኢያሱ 1፡9

"እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፥ በምትሄድባትም መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፥ ወደዚችም ምድር እመልስሃለሁ፤ የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።" ዘፍ 28፡15

"በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፥ እነሆ፥ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ።" ዘጸ 23፡20

"ነገር ግን ከዚያ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትሻላችሁ፤ በልብህም ሁሉ በነፍስህም ሁሉ የፈለግኸው እንደ ሆነ ታገኘዋለህ።" ዘዳ 4፡29

"ወደ እኔ ጩኽ፥ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ።" ኤር 33፡3

"ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፥ ተራራውና ኮረብታውም ሁሉዝቅ ይላል፤ ጠማማውም ይቃናል፥ ስርጓጕጡም ሜዳ ይሆናል፤

የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፥ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል፥የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።" ኢሣ 40፡4፣5

"አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ፤ ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ።" መዝ 32፡8

"በፊትህም የሚሄድ እርሱ እግዚአብሔር ነው ከአንተ ጋር ይሆናል፥ አይጥልህም፥ አይተውህም አትፍራ፥ አትደንግጥ አለው።" ዘዳ 31፡8

"እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው? በሚመርጠው መንገድ ያስተምረዋል።" መዝ 25፡12

"ምሕረትና እውነት ከአንተ አይራቁ፤ በአንገትህ እሰራቸው፤ በልብህ ጽላት ጻፋቸው።በእግዚአብሔርና በሰው ፊትም ሞገስንና መልካም ዝናን ታገኛለህ።" ምሳሌ 3፡5-6

"ተመካከሩ፥ ምክራችሁም ይፈታል፤ ቃሉን ተናገሩ፥ ቃሉም አይጸናም፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነውና።እግዚአብሔርም በጽኑ እጅ እንዲህ ተናገረኝ፥ በዚህም ሕዝብ መንገድ እንዳልሄድ አስጠነቀቀኝ፥ እንዲህም አለኝ፡-"ኢሣ 8፡10-11

"እንዲህም ይሆናል፤ ሳይጠሩ አመልስላቸዋለሁ፥ ገናም ሲናገሩ እሰማለሁ።" ኢሣ 65፡24

<u>የተለወጠ ልብን ሊሰጠን የተገባ ተስፋ</u>

"እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ የሚያውቅ ልብ እሰጣቸዋለሁ፤ በፍጹምም ልባቸው ወደ እኔ ይመለሳሉና ሕዝብ ይሆኑኛል እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ።" ኤር 24፡7

“በሕይወትም እንድትኖር፥ አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ እንድትወድድ አምላክህ እግዚአብሔር ልብህን የዘርህንም ልብ ይገርዛል።” ዘዳ 30፡6

“አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋለሁ።” ሕዝ 36፡26

“በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤” ፊልጲ 1፡6

“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።” 2ቆሮ 5፡17

“ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።” ገላ 2፡20

“የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።” 1ተሰሎ 5፡23፣24

<u>የሐጢአት ይቅርታን ሊሰጠን የገባልን ተስፋ</u>

“በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ።” 2ዜና 7፡14

“አቤቱ፥ አንተ መሓሪና ይቅር ባይ ነህና፥ ምሕረትህም ለሚጠሩህ ሁሉ ብዙ ነውና።” መዝ 86፡5

“ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት።” ማር 11፡25

“በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥” ኤፌ 4፡23

“በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።” 1ዮሐ 1፡9

“ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፤ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች፤ እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች” ኢሣ 1፡18

“መተላለፍህን፦ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ ኃጢአትህንም አላስብም።” ኢሣ 43፡25

“እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፦ እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡ በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና” ኤር 31፡34

“በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።” ኤፌ 1፡7

<u>በሐጢአት ላይ ድል ስለመንሳት የተሰጠ ተስፋ</u>

“ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።” 1ዮሐ 5፡4

“በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።” ሮሜ 8፡37

“ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።” 1ቆሮ 15፡57

“እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ እኔ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ፤ አበረታሃለሁ፥ እረዳህማለሁ፥ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ።” ኢሣ 41፡10

“በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤” ኤፌ 6፡16

“ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።” ገላ 2፡20

“ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።” ፊል 2፡13

“ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።” ገላ 5፡16

“የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።” ሮሜ 16፡20

“የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” ሮሜ 12፡2

“ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።” 1ዮሐ 2፡15

<u>ስለፈውስ የተሰጡ ተስፋዎች</u>

“እርሱም፦ አንተ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቀህ ብትሰማ፥ በፊቱም የሚበጀውን ብታደርግ፥ ትእዛዙንም ብታደምጥ፥ ሥርዓቱንም ሁሉ ብትጠብቅ፥ በግብፃውያን ላይ ያመጣሁትን በሽታ አላደርስብህም፤ እኔ ፈዋሽህ እግዚአብሔር ነኝና አለ።” ዘጸ 15፡26

“ጫማህ ብረትና ናስ ይሆናል፤እንደ ዕድሜህ እንዲሁ ኃይልህ ይሆናል።” ዘዳ 33፡25

“ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፤

ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፥ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፥

ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት፥ በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ፥

ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት፥ ጕልማስነትሽን እንደ ንስር ያድሳል።” መዝ 103፡2-5

“በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን፤ እግዚአብሔርን ፍራ፥ከክፉትም ራቅ፤ይህም ለሥጋህ ፈውስ ይሆንልሃል፥ ለአጥንትህም ጠገን።” ምሳሌ 3፡7፣8

“የተናቀ ከሰውም የተጠላ፥ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው፥ እኛም አላከበርነውም።
በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤ እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው።
እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።
እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።” ኢሣ 53፡3-5

“እኔ ጤናህን እመልስልሃለሁ ቍስልህንም እፈውሳለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር ማንም የማይሻት፥ የተጣለች ጽዮን ብለው ጠርተውሻልና።” ኤር 30፡17

“እነሆ፥ ፈውስንና መድኃኒትን አመጣላታለሁ፥ እፈውሳቸውማለሁ፤ የሰላምንና የእውነትን ብዛት እገልጥላቸዋለሁ።” ኤር 33፡6

“ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች፥ ፈውስም በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል፤ እናንተም ትወጣላችሁ፥ እንደ ሰባም እምቦሳ ትፈነጫላችሁ።” ሚልክ 4፡2

“ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።” ያዕቆብ 5፡14፣15

<u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ጥንካሬን ለመስጠት የገባልን ተስፋ</u>

“ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።” 2ቆሮ 4፡16-18

“ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።” ፊል 4፡13

“እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ።” 2ቆሮ 12፡9

<u>የእግዚአብሔር ምስክሮች ስለመሆን የተሰጠ ተስፋ</u>

አትፍሩ አትደንግጡም፤ ከጥንቱ ጀምሬ አልነገርኋችሁምን? ወይስ አላሳየኋችሁምን? እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ። ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም ማንንም አላውቅም።” ኢሣ 44፡8

“ብርሃንሽ መጥቶአልና፥ የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ፥ አብሪ።” ኢሣ 60፡1

“ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤” 2ቆሮ 5፡18

“እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ። ወደምሰድድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና፥ የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና። ብላቴና ነኝ አትበል።” ኤር 1፡7

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።” የሐዋ ስራ 1፡8

“እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤” 1ጴጥ 2፡9

“ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።” 1ጴጥ 3፡15

**የአስር ቀናት ጸሎት መጨረሻው ሰንበት አከባበር**

የመጨረሻውን ሰንበት የእግዚአብሔርን መልካምነትና ታላቅ ሐይሉን በማሰብ የምታከብሩት ይሁን፡፡ ባለፉት 10 ቀናት ውስጥ የጸሎትን ሐይልና የዘላለሙን ወንጌል መልካም የምስራች እንዴት ባለ ልምምድ እንዳሳለፋችሁ የምታጋሩበት ጊዜ ይኑር፡፡ እግዚአብሄር በሰራው እየሰራ ባለውና ወደፊት በሚሰራው ስራው ደስ ይበላችሁ፡፡

የእያንዳንዱ ጉባኤ ፍላጎት የተለያየ ነው፤ ስለዚህ ለራሳችሁ ቤተክርስቲያን የተለየ እቅድ መንደፍ እንድትችሉ ከአጥቢያ መሪዎች ጋር ስሩ፡፡ በመጨረሻው ሰንበት አገልግሎት ውስጥ የምታካትቷቸው ነገሮች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ጭብጥ** - የሶስቱ መላዕክት የጸሎት ጥሪ

**ጭብጡን የሚያሳይ ጥቅስ** - ራዕይ 14፡6

**ሊዘመሩ የሚችሉ የውዳሴ መዝሙሮች**

የጸሎት ሠዓት

የበረከት ዝናብ አለ

ጸጥ በሉ

**የስብከት ሐሳቦች**

ፓስተሩ፣ የቤተክርስቲያን ሽማግሌው ወይም የጸሎት መሪው የሶስቱ መላዕክት መልዕክት በዚህ መጨረሻ ዘመን እንዴት አድርጎ ወደ ጸሎትና መነቃቃት እንደሚመራን አጭር ስብከት እንዲሰብክ አድርጉ፡፡ ራዕይ 14፡6-12

የ10 ቀናቱ አገልገሎት ላይ የተሳተፉ ሰዎች  የየቀኑን መልዕክት ጠቅለል አድርገው ለ1 ወይም 2 ደቂቃ እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡ ርዕሱን፣ ዋናውን ጥቀስና ቁልፍ የሆነውን ሐሳብ ያካፍሉ፡፡ (ቀድመው በመዘጋጀት ሃሳቡን በ1 ወይም 2 ደቂቃ ይጠቅልሉ፡፡)

ሶስት ወጣቶች የሶስቱ መላዕክት መልዕክት ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት እንዴት አድርጎ ወደ ጸሎትና መነቃቃት እንደሚመራን የ 5 ደቂቃ ስብከት ያቅርቡ፡፡ ወጣቶች በምስክርነትና በሙዚቃም ሊረዱን ይችላሉ፡፡

**ሌሎች ሊካሄዱ የሚችሉ ፕሮግራሞች**

ስለተመለሱላቸው ጸሎቶቻቸው አባላት የሚሰጡት ምስክርነት

የትናንሽ ቡድን የጸሎት ጊዜ

ወደፊት የጸሎቱን ጊዜ እንዴት ማስቀጠል እንደሚቻል ማስታወቂያ

ስለጸሎት የሚናገር የልጆች ታሪክ

የተለዩ መዝሙሮችን መርጦ መዘመር

የአለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የጸሎት ጥያቄዎች ላይ መጸለይ

ጌታ ሆይ እባክህን በፍጻሜ ዘመን ውስጥ አንተን የመምሰል ታላቅ መነቃቃት ቤተክርስቲያንህን ያጥለቅልቅ፡፡ ሰማይ ቢገለበጥም ለእውነትህ እንድንቆም አስችለን፡፡

በአለም ዙሪያ ለሐይማኖት ነጻነትና ለህሊና ነጻነት መስፋፋት እንጸልያለን፡፡ ጌታ ሆይ ቃልህ የሚሰበክበትን በር ሁሉ ክፈትልን፡፡

ጌታ ሆይ ያንተ አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን የሶስቱን መላዕክት ለነገድና ለቋንቋ በሰፊው እንድትሰብክ የቀረበላትን ጥሪ እንድትቀበል እርዳት፡፡  ጌታ ሆይ የክርስቶስና ፍቅርና ጽድቅ እንዴት አድርገን የነዚህ ትምህርቶች ሁሉ ማዕከል እንደምናደርጋቸው አሳየን፡፡

ጌታ ሆይ በአለም ያሉ አድቬንቲስቶች “እሄዳለሁ” ብለው በማወጅ አንተን የማገልገልን ጥሪ እንዲቀበሉና የድነትን መልካም ዜና እንዲያበስሩ እርዳቸው፡:፡

የእግዚአብሔርን ቃል ለመመርመር፣ ለመረዳትና ለመከተል ጥበብ እንድትሰጠን እንጸልያለን፡፡ ቃልህን በትክክል እየገለጽን ለሌሎች በታማኝነት እንድናካፍል እርዳን፡፡

ጌታ ሆይ እባክህን በኤለን ኋይት ጽሆፎች ውስጥ ለሚገኙትን ሰማያዊ መመሪያዎች ያለንን አድናቆት አድስልን፡፡

የመንፈስ ቅዱስ የኋለኛው ዝናብ ለምስክርነታችን ሐይል እንዲሰጥና ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት አንተ የሰጠኸንን ስራ እንድንጨርስ ትረዳን ዘንድ እንጸለያለን፡፡

በኮቪድ 19 እጅጉን ለተጠቁ ስፍራዎች የአንተ ፈውስና ምህረት እንዲመጣ እንጸልያለን፡፡

በሚወስኗቸው ውሳኔዎች ጥበብን ትሰጣቸው ለሐኪሞች፣ ሳይንቲስቶች፣ የመንግስት መሪዎችና ለጤና ባለሙያዎች ዘንድ አንለምንሃለን፡፡

በአለም ዙሪያ ያሉ አድቬንቲስቶች ለሚሰቃዩት ድጋፍና ማበረታቻን መስጠት እንደችሉ እንድትረዳቸው እንጸልያለን፡፡ ጎረቤቶቻችን በጣም በፈለጉን ጊዜ ድፍረትን፣ ጥበብንና ራስወዳድነት የሌለበትን መንፈስ ስጠን፡፡

ስራ በማጣትና መስሪያ ቤቶች ከመዘጋታቸው የተነሳ በገንዘብ ማጣት ስለተጎዱት እንጸልያለን፡፡

ጌታ ሆይ እባክህ በአእምሮ ህመምና በብቸኝነት የተጎዱትን እንዴት ማገልገል እንደሚችሉ ለአባሎቻችን አሳያቸው፡፡

የስራ ቦታዎች ዝግ በሆኑበት ጊዜ ፓስተሮችና ቤተክርስቲያኖች አባሎችን መጠበቅ እንዲችሉ እንጸልያለን፡፡ ጌታ ሆይ እባክህ ቤተክርስቲያንህን በአምልኮና በአገልግሎት አያይዘህ ጠብቅልን፡፡

በአለም ዙሪያ በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙ ተማሪዎቻችን መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲኖራቸው እንጸልያለን፡፡ ለክርስቶስ ንቁ አምባሳደሮች እንዲሆኑ እርዳቸው፡፡

የክርስቶስን ግልጽ የሆነ መልዕክት ላልተቀበሉ 69 በመቶ ለሆኑ የአለም ህዝቦች እንጸልያለን፡፡

28 ወንጌል ያልገባባቸው ከተሞች ውስጥ ለሚገኙ 62 ሚሊዮን ለሚሆን የቀድሞ የሶቪየት ዩኒየን ነዋሪዎች (ለዩሮ ኤዥያ ዲቪዥን) እንጸልያለን፡፡

በመካከለኛ ምስራቅ 20 ሐገሮች ውስጥ ለሚገኙ 746 ነገዶች የወንጌልን ስራ ለመስራት ፈቃደኛ የሚሆኑ ሚሲዮናውያንን እንድታስነሳ እንጸልያለን፡፡

ሌሎችን በመውደድና በሌላ ባህልና እምነት ውስጥ ላሉ ሰዎች ወንጌልን የሚያጋራ ታላቅ የአድቬንቲስት ሰራዊት ኀርፍ እንድታስነሳ እንጸልያለን፡፡

ጌታ ሆይ እባክህን በአስቸጋሪ ስፍራም ቢሆን የሚያገልግሉህን ዘመናዊ የዋልደንስ ተማሪዎችን አስነሳልን፡፡

በእምነታቸው ምክንያት ስደትና መታሰር ለደረሰባቸው አድቬንቲስቶች እንጸልያለን፡፡

በደቡባዊ ኢሲያ ፓሲፊክ ዲቪዥን ባልተገባባቸው 41 ከተሞች ውስጥ ለሚገኙ 202 ሚሊዮን ሰዎች ጌታ ኢየሱስን ያውቁ ዘንድ እንጸልያለን፡፡

የየኢጥቢያ ቤተክርስቲያን የግል ወንጌል አገልግሎት ወይም የሰንበት ትምህርት አገልግሎት ዘርፎች የእግዚአብሔርን እቅድ በመፈለግ በፍቅር አገልግሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥትና የግል ምስክርነት የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ ለመድረስ ስለሚያደርጉት ጥረት እንጸልያለን፡፡

የአድቬንቲስት ልማትና እርዳታ ድርጅት (አድራ) በአለም ዙሪያ የሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት ስለሚያደርጉት ጥየት እንጸልያለን፡፡

በምዕራብ ፓሲፊክ ዲቪዥን ውስጥ በጥቂቱ በተደረሱ 6 ከተሞች ውስጥ ለሚገኙ 16 ሚሊዮን ሰዎች እንጸልያለን፡፡

በሰሜናዊ ኢስያ ዲቪዥን ውስጥ በጥቲቁ በተደረሱ 105 ከተሞች ውስጥ ለሚገኙ 406 ሚሊዮን ህዝቦች እንጸልያለን፡፡

ጌታ ሆይ እባክህን የቻፕሌንሲ አገልግሎት ክፍልና ፍላጎት ያላቸው አባላት በወህኒ ቤቶች ያሉትን ለማገልገል ሲንቀሳቀሱ እንድትባርካቸው እንጸልያለን፡፡

ጌታ ሆይ ለሰንበት ትምህርት መምህራኖቻችን እንጸልያለን፡፡ ለልጆች መስራታቸው ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንዲያውቁ ፈቃድህ ይሁን፡፡

ጌታ ሆይ በአለም ዙሪያ ለሚገኙ ለተጽእኖ ፈጣሪ ማዕከሎች፣ ለጤናና ቤተሰብ መርሀ-ግብሮች እንዲሁም ለጎዳና ፈላጊ ክለቦች ያንተን አመራር እንጠይቃለን፡፡

አዳዲስ አባላትና ጎብኚዎችን አንድንወድ፣ እንድንንከባከብና ደቀመዝሙር እንድናደርግ እንድትረዳን እንጸልያለን፡፡

ጌታ ሆይ ይበልጥ በእውነት የተሞሉ ጸሁፎችን እንዴት አድርገን ወደ ማህበረሰበቡ እንደምናደርስ አሳየን፡፡፡ ሰዎች እንዲያነቡትና የቀሉን እውነት መቀበል እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳቸው እንጸልያለን፡፡

በአደገኛ ቦታዎች ለሚሰሩ ሚሲዮናውያን ጥበቃህ እንዳይለያቸው እንጠይቅሃለን፡፡

እባክህን የተስፋና የህይወት ቃላትን ያሰራጩ ዘንድ የጽሁፍ ወንጌላውያንን፣ ፈቃደኛ ተማሪዎችን፣ ጸሐፊያንን፣ የሚዲያ ባለሙያዎችን እንዲሁም በገንዘብ የሚደግፉትን አስነሳልን፡፡

በአለም ዙሪያ ላሉ የአድቬንቲስት ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎችና መምህራን እንጸልያለን፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች በታማኝነት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት እንዲያስተምሩና ወጣቶችን ወደ ተልዕኮ፣ አገልግሎትና ከክርስቶስ ጋር ወደሚኖራቸው የሚያድን ግንኙነት እንድትታደርሳቸው እንጸልያለን፡፡

ለሐይማኖት ፍላጎት የሌላቸውን አለማዊ ባህሎች መድረስ እንድንችል ጥበብን ስጠን፡፡ አለማዊ ልቦችን የከበበውን ግድግዳ መንፈስ ቅዱስ ይደረምስ ዘንድ እንጸልያለን፡፡

በጥንቆላ፣ በጣኦት አምልኮና ተፈጥሮን በማምለክ ባርነት ውስጥ ላሉ ህዝቦች መድረስ እንድንችል ባርከን፡፡ ንጽረተ-አለማቸውን መረዳትና ከግል አዳኛቸው ጋር ማስተዋወቅ እንድንችል እርዳን፡፡

ጌታ ሆይ በአለም ዙሪያ ያሉ አድቬንቲስቶች ከዚህ በፊት ጸልየው በማያውቁት መንገድ እንዲጸልዩ አነቃቃቸው፡፡ ስንጸልይ ተራሮችን እንደምትንድ እየጠበቅንና ተስፋህንም እየጠየቅን እንዲሆን አስተምረን፡፡

በደቡባዊ አፍሪካ-ኢሲያ ዲቪዥን በ18 ሐገሮች ውስጥ ለሚገኙ 541 ጎሳዎች እንጸልያለን፡፡ እባክህን ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ምራቸው፡፡

የስደተኞችን መንፈሳዊና አካላዊ ፍላጎቶች እንዴት እንደምናሟላ አሳየን፡፡ ቤተክርስቲያናችን ምንም አይነት ሰዎች ቢሆኑ፣ ከየትም ስፍራ ቢመጡ ለእነርሱ ባለን ፍቅር የታወቀች እንድትሆን ፈቃድህ ይሁን፡፡

በኢንተር ዩሮፒያን ዲቪዥን 20 ሐገሮች ውስጥ በሚገኙ 806 ጎሳዎች መካከል ቤተክርስቲያናትን ለማሟቋም የሚንቀሳቀሱ የከተማ ሚሲዮናውያንን እንድታስነሳልን እንጠይቃለን፡፡

በኢንተር-አሜሪካ ዲቪዥን 38 ሐገሮች ውስጥ በሚገኙ 948 ጎሳዎች መካከል ቤተክርስቲያናትን የሚያቋሙ የሰራተኞችን ሰራዊት እንድታስነሳ እንጸልያለን፡፡

መሰረታዊ የቤተክርስቲያን እምነቶቻችንን በግልጽ፣ በመነቃቃትና የእግዚአብሔርን ቃል ስልጣን በመጠበቅ እንዴት እንደምናውጅ አስተምረን፡፡ የምናምነው ነገር መሰረቱ የክርስቶስ ፍቅር እንዲሆንም እርዳን፡፡

በሰሜን አሜሪካ ዲቪዥን 9 ሐገሮች ውስጥ በሚገኙ 789 ጎሳዎች መካከል ቤተክርስቲያንን ለማቋቋም ወጣቶችን እንድታዘጋጅ እንለምንሃለን፡፡

በእስራኤል ፊልድ በሚገኙ 70 ጎሳዎች መካከል በፈቃድ የሚያገለግሉትን እንድታዘጋጅ እንለምንሃን፡፡

በመካከለኛው-ምስራቅ አፍሪካ ዲቪዥን 11 ሐገሮች ውስጥ በሚገኙ 830 ጎሳዎች መካከል ቤተክርስቲያናትን የሚያቋቁሙ የህክምና ሚሲዮናውያንን እንድታስነሳ እንጸልያለን፡፡

በደቡባዊ ኢስያ ዲቪዥን 4 ሐገሮች ውስጥ ለሚገኙ 2585 ቡድኖች/ወገኖች/ የሚማልዱ የጸሎት ተዋጊዎችን እንድታስነሳ እንጸልያለን፡፡

እባክህን ቤተሰቦቻችን በቤታቸውና በማህበረሰባቸው ውስጥ ያንተን ፍቅር እንዲገልጹ ፈቃድህ ይሁን፡፡ በቤቶች ውስጥ ስምምነቶችን እንድታመጣ፣ የተበላሹ ግንኙነቶችን እንድትፈውስ፣ ለጥቃት የተጋለጡትን እንድትጠብቅና ተስፋ የሌለው በሚመስል ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ የሚቀድሰውን ሐይልህን እንድትሰጥ እንለምንሃለን፡፡

በምዕራባዊ-መካከለኛ አፍሪካ ዲቪዥን 22 ሐገሮች ውስጥ ለሚገኙ 1976 ቡድኖች/ወገኖች/ መካከል ቤተክርስቲያናትን ማቋቋም የሚችሉ ነርሶችና ዶክተሮች እንድታስነሳ እንጸልያለን፡፡

በትራንስ ዩሮፒያን ዲቪዥን በጥቂቱ በወንጌል የተደረሱ 19 ከተሞች ውስጥ ለሚገኙ 49 ሚሊዮን ህዝቦች እንጸልያለን፡፡

ለልጆቻችን እንጸልያለን፡፡ አቤቱ እንቅፋትና ጫና ሲበዛባቸው ለአንተ በድፍረት እንዲቆሙ አስታጥቃቸው፡፡ ጥበብ የተሞላበት ምርጫ እንዲመርጡና ለእውነት እንዲቆሙ እርዳቸው፡፡

በቅርባችን ላሉ ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንድንችል የክርስቶስን ራስ ወዳድነት የሌለበት ምሳሌነት እንድንከተል አስተምረን፡፡ የህክምና ሚሲዮናውያን፣ ማህበረሰብን በፈቃድ የምናገለግልና ለተቸገሩ ወዳጆች ሆነን እንድናገለግል አስታጥቀን፡፡

የቤተክርስቲያንን ቅርስ (በክርስቶስ ያገኘነውን ማንነት፣ እንደአድቬንቲስት የተሰጠንን ተልዕኮ፣ እንዲሁምበአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን አመራር) ለቀጣዩ ትውልድ ለሚያስተላልፉ በአለም ዙርያ ላሉ የወጣት መሪዎች እንጸልያለን፡፡

በአንድ አመት አገልግሎትና በካሌብ ተልዕኮ ውስጥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ለጌታ እየሰሩ ላሉ ወጣቶች እንጸልያለን፡፡

በአለም ዙሪያ ያሉ አባሎቻችን፣ ፓስተሮችና መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል በየእለቱ እንዲመገቡ እርዳቸው፡፡ እኛም በየእለት ጸሎት አንተን መፈልግ እንድንችል እርዳን፡፡ ያለ አንተ ምንም ማድረግ እንደማንችል ሁልጊዜ አስታውሰን፡፡

## 1ኛ ቀን- የጸሎት አስፈላጊነት

በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸዋል? ሉቃ 11፡13

**ተስፋ አስቆራጭ የሚመስለው ስራ**

የዓለም ህዝብ እየጨመረ ነው። የቅርብ ጊዜ የሕዝብ ቁጥር መረጃዎች እንደሚያሳዩት በሰአት 67,000 ማይል ርቀት በሚዓዘው ጠፈር ላይ የምትሽከረከረው ምድራችን ውስጥ ወደ 7.8 ቢሊዮን የሚጠጉ ሰዎች ይኖራሉ። በየቀኑ በግምት 385,000 ሕፃናት ፣ ወይም በየዓመቱ 140 ሚሊዮን ሲወለዱ ፣ እኛ በወንጌል ምሥራች እና በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት መልዕክት እንዴት ወደዚህ ዓለም እንደምንደርስ እናስባለን። በአሁኑ ጊዜ የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አባላት ከሆኑት ሰዎች በሰባት እጥፍ ያህል በየአመቱ ሰዎች ይወለዳሉ።

ወይም ፈተናውን በሌላ መንገድ እናስበው። የዓለም ከተሞች በፍጥነት እያደጉ ናቸው። አንድ ሚሊዮን ወይም ከዚያ በላይ ሕዝብ ያላቸው ቢያንስ 548 ከተሞች አሉ። አብዛኛዎቹ እነዚህ ከተሞች የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን በጣም ጥቂት በሆነባቸው አገሮች ውስጥ የሚገኙ ናቸው። ከሦስቱ መላእክት መልእክቶች ጋር ወደዚህ ዓለም የመድረስ ከባድ ሥራ እንደቀጠለ ነው። ሚሊዮኖች ያለ ክርስቶስ፣ የመዳን የምሥራች እና የዳግም ምጽዓቱን ተስፋ ሳይረዱ እየሞቱ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከፊታችን ያለው ተግባር የማይቻል ይመስላል - እናም ይህ በጉልበታችን ተንበርክከን ከልብ ወደመጸለይ ሊያንቀሳቅሰን ይገባል።

**በመንፈስ ቅዱስ ኃይል**

ስለክርስቶስ በማሳወቅ ዓለማችንን ለመድረስ ምንም ዓይነት የሰው ጥረት በቂ አይደለም። የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እስካልሰጣቸው ድረስ የሰው ዕቅዶች ኃይል የላቸውም። ይህ ሰማያዊ የመጨረሻ ዘመን መልእክት ወደዓለም የሚደርሰው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። በዚህ ዓለም ታላላቅ ከተሞች ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩት ሰዎች በወንጌል ሊደረሱ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። ወንጌልን የሚቃወሙ፤ ወንጌልን ለማዳረስ የማቻልባቸው አገሮች ሊደረሱ የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። ማህበረሰባችን ሊደረስ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። የምስራቹ ዜና እግዚአብሔር ቀድሞውኑ በእነዚህ "ለመድረስ አስቸጋሪ" በሆኑ ቦታዎች ውስጥ እየሠራ መሆኑ ነው። ከፊታችን ያለውን ተግባር የመፈጸም ኃይልን እንዲሰጠን እርሱን እንድንፈልግ ይጋብዘናል።

**ምን ያህል አብልጦ**

ኢየሱስ “እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ ፣ የሰማይ አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸዋል” (ሉቃስ 11:13)። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ “ምን ያህል አብልጦ” የሚለውን አገላለጽ ልብ ይበሉ። ኢየሱስ እኛ ከምናስበው በላይ ለእኛ እና ለቤተክርስቲያኑ ብዙ ነገር ለማድረግ ይፈልጋል። መንፈስ ቅዱስን እንድንለምን ፣ መንፈሱን እንድንሻው ፣ የመንፈስን በረከት በፍጹም ልባችን እንድንፈልግ ያሳስበናል - ያልተቀበልነው እሱ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ሳይሆን እኛ ለመቀበል ዝግጁ ስላልሆንን ነው። በዚህ ዓመት እነዚህን አስር የጸሎት ቀናት ስንጀምር ፣ ተስፋ ኪዳን አብረን እንጠይቅ።

“የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ በማንኛውም ዕድሜ ወይም ዘር የተወሰነ አይደለም። የመንፈሱ መለኮታዊ ተጽዕኖ እስከ መጨረሻው ድረስ እርሱን ከሚከተሉት ሰዎች ጋር እንደሆነ ክርስቶስ ተናግሯል። ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ራሳቸውን ለጌታ ሙሉ በሙሉ ለሰጡ ሁሉ አጽናኙ መንፈስ ተልኳል” (the acts of appostles፣ ገጽ 49)።

አብረን እንጸልይ።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**ከ 2021 የአስር ቀናት የጸሎት ጊዜ በኋላ የተሰጠ ምስክርነትን እናስታውስ**

“ለአሥሩ የጸሎት ቀናት አመሰግናለሁ። በእኔ ውስጥ እሳት እንደተቀጣጠለ ይሰማኛል። መጽሐፍ ቅዱስ በማንበብ እና ከጌታ ጋር በመሆን ብዙ ጊዜ አሳልፋለሁ። . . .ኢየሱስን እና መንፈስ ቅዱስን በሕይወቴ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ዓይኖቼን ፣ ልቤን እና አዕምሮዬን ስለከፈተልኝ እግዚአብሄርን አመሰግናለሁ ።(ኮንስታንስ)

**ታላቅ ተስፋ**

“ከእናንተ ሁለቱ በምድር ተስማምተው የሚለምኑት ሁሉ ፤ በሰማያት ካለው ከአባቴ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና (ማቴዎስ 18: 19, 20) ‘ጠይቀኝ ፣ ጥያቄዎችህን እመልስልሃለሁ።’ የተገባው የተስፋው ቃል፡- **የቤተክርስቲያኑ አንድነት ጸሎቶች በሚጸለዩበት ጊዜ ለእነዚህ ጸሎቶች መልስ በግል ጸሎት ከሚመጣው መልስ የበለጠ ኃይል**

**ይጠበቃል። የተሰጠው ኃይል ከአባላቱ አንድነት፤ ለአምላክ እና እርስ በእርስ ካላቸው ፍቅር ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል** ”(ኤለን ጂ. ኋይት ፣ manuscript releases፣ ቅጽ 9 ፣ ገጽ 303)።

**ሁሉም የጸሎት ቡድኖች አብረው የሚጸልዩበት የተለያዩ መንገዶች አሏቸው። መንፈስ ቅዱስ በሚመራበት በማንኛውም መንገድ በሚቀጥሉት 30-45 ደቂቃዎች ውስጥ በአንድነት ጸሎት እንዲያሳልፉ እናበረታታለን። መጽሃፍ ቅዱስን በማጣቀስ ለመጸለይ የሚረዱ ጥቅሶች ከዚህ በታች አሉ። ሌሎች ምእራፎችን በመጥቀስ መጸለይ ይችላሉ። ለሌሎች የጸሎት ሀሳቦች “የመሪዎች መመሪያ” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።**

**የእግዚአብሔርን ቃል እየጠቀሱ መጸለይ - ሉቃስ 11:13**

“በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸዋል!”

**“ምን ያህል”**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ እጅግ በጣም አፍቃሪ ከሆነው ወላጅ በላይ እንኳን አንተ መልካም ነህ፤ የእኔን መልካም ነገር ትመኛለህ። ውስጣዊ ማንነቴን እና ልቤን ታውቃለህ ፣ ስለዚህም እንዴት እንደምትመልስልኝ ፣ እንደምትፈውሰኝ እና እንደምትለውጠኝ አንተ ብቻ ታውቃለህ።

**“መንፈስ ቅዱስ”**

ኢየሱስ ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ተስፋ አመሰግናለሁ። እርሱ የእግዚአብሔርን በረከቶች ወደ ሕይወታችን ያመጣል። በልባችን ያከብርሃል። እርሱ በቀራንዮ ላይ የሠራኸውን የማዳን ስራ በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል። ለዚህ ስጦታ እናመሰግናለን!

**“ማነው የሚጠይቀው”**

አባት ሆይ ፣ ዛሬ የሉቃስ 11፡13 ተስፋን እጠይቃለሁ። በየቀኑ ሕይወቴን አሁን ባለው ፣ በመንፈስ ቅዱስ መገኘት እና ኃይል እንድትሞላ በደስታ እጠይቅሀለሁ። ራሴን ለአንተ እንዳላስረክብ እንቅፋት የሚሆነውን ነገር ሁሉ አንተ ከህይወቴ አስወግድ። አንተን በሚፈልግ ዓለም ውስጥ እንድናስከብርህ እኔ እና ቤተክርስቲያኔን በመንፈስ ቅዱስ አጥምቅ።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

- ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።
- መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።
- መመሪያ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።
- ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።
- የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።
- አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

**ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች**

የ ውዳሴ መዝሙር

የጸሎት ሰአት (63)

ጌታ ጽዋዬን ሙላ (76)

ጸጥ ጸጥ በሉ (25)

## 2ኛ. ቀን - ዘለአለማዊው ወንጌል እና ፀሎት

ከዚህ በኋላ በምድር ላይ የሚኖሩ ህዝብ ፣ ነገድ ፣ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ለሚናገሩ ለተለያዩ ወገኖች ሁሉ ለማብሰር ዘለአለማዊውን ወንጌል የያዘ ሌላ መልአክ በሰማይ ሲበር አየሁ። የዮሃንስ ራእይ 14 ፡ 6

**እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ መልእክት**

እግዚአብሔር በራእይ 14 6-12 በሦስቱ መላእክት መልእክቶች ውስጥ በተለይ ለጊዜያችን የተዘጋጀ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ መልእክት ለዚህች ፕላኔት ሰጥቷል። በፍጥሞ ደሴት ላይ ተሰዶ ሳለ ሐዋርያው ዮሐንስ እነዚህን መልእክቶች ይነግረናል። መልእክቱን እራሱ ከማየታችን በፊት ሦስት ነጥቦችን በጥንቃቄ ማጤን አለብን።

<u>በመጀመሪያ</u> , ይህ መልእክት መነሻው ከመለኮት ዘንድ ነው። በቀጥታ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዙፋን ነው። በሰማይ መካከል በሚበር መልአክ ለሰው ልጅ እንደተሰጠ ተደርጎ ተገልፆአል።

<u>በሁለተኛ ደረጃ</u> - ስለዚህ መልእክት ልብ ሊባል የሚገባው ሁለተኛው ነጥብ መልአኩ "መብረሩ" ነው። ይህ መልዕክት አስቸኳይ ነው። ሳይዘገይ መታወጅ አለበት።

<u>በሶስተኛ ደረጃ</u> - መልዕክቱ ለእያንዳንዱ ትውልድ የሚሆን ዘላለማዊ መልእክት ነው። በባህላዊ ሁኔታ ወደ አንድ ጎሳ ወይም የቋንቋ ቡድን ብቻ የሚደርስ አይደለም። "ለሕዝብ ፣ ለነገድ ፣ ለቋንቋና ለሕዝብ ሁሉ" መሰበክ አለበት።

የዚህ መልእክት ዋና ምሰሶው "የዘላለም ወንጌል" ወይም የክርስቶስ ሕይወት ፣ መሥዋዕትነት ፣ የፍቅር አገልግሎቱን ፣ የኃጢያት ክፍያ የሆነው ሞቱን ፣ አስደናቂ ትንሣኤውን ፣ የምልጃውን ሊቀ ካህንነት አገልግሎቱን ፣ እና በክብር ዳግም መምጣቱ ምሥራች ነው። በራእይ 14 ላይ ያለው የዘላለም ወንጌል ራዕይ በማቴዎስ 24 ላይ የኢየሱስን ቃላት ያረጋግጣል - "ለህዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚአብሄር መንግስት ወንጌል በመላው አለም ይሰበካል ፤ በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል።" (ማቴዎስ 24:14) ). የክርስቶስ ቃል፤ እርሱ ዳግም ከመምጣቱ በፊት "ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል" የሚል ተስፋ ነው። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ታላቅ መነቃቃት ይኖራል። እነሱ ወደ ፈተናው ይገባሉ ፣ የሰዓቱን አጣዳፊነት

ይገነዘባሉ ፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ፣ በኃጢአት ለተበከለው እና ለሚሞተው ዓለም የኢየሱስን ፍቅር ፣ ጸጋ እና እውነት ይገልጣሉ።

ኤለን ኋይት በዚህ መንገድ ትገልጸዋለች ፣ “የእግዚአብሔር ፍርድ በምድር ላይ ከምጣቱ በፊት ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ያልታየው የቀድሞው እግዚአብሔርን የመምሰል ሁኔታ በጌታ ሰዎች መካከል ይኖራል። የእግዚአብሔር መንፈስ እና ኃይል በልጆቹ ላይ ይፈሳል። በዚያን ጊዜ ብዙዎች የእግዚአብሔር እና የቃሉ ፍቅርን በዚህ ዓለም ፍቅር ከለወጡባቸው ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ይለያሉ። ብዙዎች ፣ አገልጋዮችም ሆኑ ሰዎች ፣ ለጌታ ዳግም ምጽዓት ለማዘጋጀት እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ እንዲታወጅ ያደረጋቸውን ታላላቅ እውነቶች በደስታ ይቀበላሉ” (GC, 464)።

የዮሐንስ ራእይ 14 መልእክት ለዓለም ሁሉ ከመታወጁ በፊት በእግዚአብሔር ሕዝቦች መካከል መንፈሳዊ መነቃቃት ሥራውን በማጠናቀቅ ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር ያስችላቸዋል። ለመጨረሻው ዘመን አስከፊ ሁኔታዎች ራሳችንን ለማዘጋጀት በሕይወታችን ውስጥ መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲመጣ አብረን እንጸልይ ።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**ከ 2021 የአስር ቀናት የጸሎት ጊዜ በኋላ የተሰጠ ምስክርነት ትውስታ**

“አስርቱ የጸሎት ቀናት ለእኔ የፈውስ ተአምራትን አሳይተውኛል። አስሩ የጸሎት ቀናት ከመጀመሩ በፊት በድንገተኛ ሕመም ምክንያት ሆስፒታል ገባሁ። ሁኔታዬ በየቀኑ እየተባባሰ ስለመጣ ጸሎቴ በቂ እንዳልሆነና ተስፋ እንደሌለኝ ተሰማኝ። በሆስፒታል አልጋዬ ላይ አስሩን የፀሎት ቀናት እንድቀላቀል ተጋበዝኩ። ያኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ስሳተፍ ነበር። በሌሊት በሚደረጉ የዙም የቪዲዮ ስብሰባዎች በኩል ብዙዎች ለፈውሴ ጸለዩልኝ። ለእያንዳንዱ የጸሎት ጥያቄያችን በየምሽቱ አጥብቀው ስለሚጸልዩ አስደናቂ ነፍሳት እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። . . .አሥር የጸሎት ቀናት ከማለቃቸው በፊት ተፈወስኩኝ ፣ እግዚአብሔር ቸርነት አድርጎልኛል። እኔን ያዳነኝ የፈውስ ኃይሉ ነው። ታምሜ ሳለሁ እሱ ነካኝ። በእርግጥም ለጸሎት የተሰጠ መልስ ነበር! ” (ሃርሊ)።

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ - ራእይ 14: 6**

“ከዚህ በኋላ በምድር ላይ ለሚኖሩ ህዝብ ፣ ነገድ ፣ ልዩ ልዩ ቃንቃዎችን ለሚናገሩ ለተለያዩ ወገኖች ሁሉ ለማብሰር ዘለአለማዊውን ወንጌል የያዘ ሌላ መልአክ በሰማይ መካከል ሲበር አየሁ።"

**“የዘላለም ወንጌል”**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ በወንጌል መልእክት አማካኝነት ሁልጊዜ እያደገ የመጣ ደስታ ስጠኝ። የመዳንን ደስታ ስጠኝ። ሌሎች እኔን ሲያዩኝ ፣ የወንጌልን ኃይል በሥራ ላይ እንዲያዩ እና ወደ ኢየሱስ እንዲሳቡ ሕይወቴን ለወጠው።

**“በምድር ላይ ለሚኖሩት ሰዎች ለመስበክ”**

አባት ሆይ ፣ ይህንን የምሥራች በቃል እና በተግባር ለሌሎች የማካፈል ልምምድን ከአንተ ጋር መለማመድ እፈልጋለሁ። በእኔ ተጽዕኖ ውስጥ ላሉት ቤተሰቦቼ ፣ ጓደኞቼ ፣ የሥራ ባልደረቦቼ ፣ ጎረቤቶቼ እና ሰዎችን ለመመሥከር እኔን ተጠቀም።

**“ለሁሉም ብሔር”**

ይህ ዓለም ወደ ፍጻሜ እየመጣ ነው ፣ እናም በቢሊዮን የሚቆጠሩ በጨለማ ውስጥ ናቸው። ኢየሱስ ፣ በዚህ ሳምንት የማዳንህን የምሥራች ለሌላ ሰው ለማካፈል እንድችል ዕድል ስጠኝ። ለሌሎች ብሔሮች ፣ ለባህላዊ አስተዳደግ እና ለጎሳ ሰዎች የምመሰክርበትን ዘዴና ጥበብ ስጠኝ። እያንዳንዱን ሰው በአንተ እንዲያምን ስለጠራህ አመሰግናለሁ።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - በግል ለመናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

ስለእግዚአብሔር አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ስለ ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጥ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች

የ ውዳሴ መዝሙር

የጸሎት ሰአት (63)

የሰስ የኔ ነው (137)

## 3ኛ. ቀን — የእግዚአብሔር ተልእኮ እና ጸሎት ፣ ክፍል 1

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ሃይልን ትቀበላላችሁ ፤ በዚያን ጊዜ በእየሩሳሌም፣ በይሁዳ ምድር ሁሉ በሰማርያ እስከምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።” (የሐዋርያት ሥራ 1: 8)

### የማይቻል ለሚመስለው ተልዕኮ የተሰጠው ተስፋ

የሦስቱ መላእክት መልእክቶች ወደ ተልዕኮ የሚያስገቡ አስቸኳይ መልእክቶች ናቸው። በወንጌል ዓለምን ለመድረስ የማይቻል የሚመስለው ተግባር የሚቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው። በመጨረሻው ዘመን ያለው የተልዕኮ ፈተና ፤ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ካጋጠማት ፈተና ጋር ተመሳሳይ ነው። **በሐዋርያት ሥራ 1፡ 8** ላይ “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ” በኢየሱስ በተሰጣቸው ተስፋ እና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ፣ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን በዓለም ላይ ተጽዕኖ አሳደረች። በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ክርስቶስን እንደ መሲሕ ተቀብለው ተጠመቁ።

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ፤ የምትጸልይ ቤተክርስቲያን እና በመንፈስ ቅዱስ የምትመሰክር ቤተክርስቲያን በሆኑት መካከል ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ይገልጻል። የሐዋርያት ሥራ 1፡14 “እነዚህ ሁሉ ዘወትር ለጸሎት በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር” ይላል። በሐዋርያት ሥራ 2፡42 ላይ “እነርሱም የሀዋርያትን ትምህርት በመስማት ፣ በህብረት በመኖር ፣ ማእድ አብሮ በመብላትና በጸሎት ይተጉ ነበር።” ይላል። የሐዋርያት ሥራ 4፡31 “ጸሎት ከጨረሱም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ ፤ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ፤ የእግዚአብሄርንም ቃል በድፍረት ተናገሩ።" በዚህ የመጨረሻ ጥቅስ ውስጥ ሦስት ነገሮችን ልብ እንበል። አማኞቹ ጸለዩ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ ፣ እናም ውጤቱ የእግዚአብሔርን ቃል በድፍረት ወይም በልበ ሙሉነት ተናገሩ። ጸሎት ፣ መንፈስ ቅዱስ ፣ እና ተልዕኮ የተባበሩ ናቸው።

### ይህ ሊኖረን ይገባል

ኤለን ኋይት በደቀ መዛሙርቱ ተሞክሮ ላይ አስተያየት ስትሰጥ ፣ “ደቀ መዛሙርቱ በበዓለ ሃምሳ ቀን እንደጸለዩት ለመንፈስ ቅዱስ መውረድ አጥብቀን መጸለይ አለብን። በዚያ ጊዜ እነርሱን አስፈልጓቸው ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ለእኛም የበለጠ ያስፈልገናል ”(5T, 158)። እንዴት ያለ መለኮታዊ ማስተዋል! ደቀ መዛሙርቱ

በወንጌል ዓለምን ለመድረስ የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ ካስፈለጋቸው እኛ ደግሞ በዚህ ጊዜ የበለጠ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያስፈልጋል። ዓለም ዛሬ ትልቅ ፣ የተወሳሰበች እና አምላክ የለሽ ነች።

ከጸሎት ውጪ በሌላ መንገድ ማድረግ የማይቻልን ነገር ለማድረግ ያለገደብ የመንፈስን ኃይል እንዲሰጠን በጸሎት እግዚአብሔርን የምንፈልግበት ጊዜ ነው። ኤለን ኋይት እንዲህ ስትል ጽፋለች ፣ “በቤተክርስቲያን ላይ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ወደፊት ይሆናል ተብሎ በጉጉት ይጠበቃል ፣ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ፤ አሁን የማግኘት መብት አላት። ፈልጉት ፣ ጸልዩለት ፣ እመኑበት። ሊኖረን ይገባል ፣ እናም ሰማይም ደግሞ እርሱን ለመስጠት እየጠበቀ ነው” (Ev, 701)።

በዚህ ትውልድ ውስጥ የሦስቱ መላእክት መልእክቶችን አዋጅ ለመፈጸም ሁላችንም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንፈልግ። ለዚህ ታላቅ ለሆነው የመንፈሱ መፍሰስ እግዚአብሔርን በጸሎት እንፈልግ።

የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)

**ከ 2021 የአስር ቀናት የጸሎት ጊዜ በኋላ የተሰጠ ምስክርነት**

"በዚህ ዓለም ነገሮች ውስጥ ደስታን ለማግኘት በመሞከር ብዙ የጎልማሳነት ሕይወቴን አሳልፌያለሁ። ትክክለኛውን ሰው እና ትክክለኛውን ሥራ ካገኘሁ እንዲሁም ደግሞ ክብደቴን መቀነስ ከቻልኩ በመጨረሻ ደስታዬን አገኛለሁ ብዬ ለራሴ ደጋግሜ እናገር ነበር። ራሴን ለዚህ ዓለም መሠዊያዎች ባቀረብኩ ቁጥር የመዳከምና የባዶነት ስሜት እንደሚሰማኝ ብዙም አልገባኝም ነበር። እኔ ሁልጊዜም የአስር ቀናት የጸሎት መምሪያዎችን በኢሜል እቀበላለሁ ፣ ግን በሐቀኝነት የአሥር ቀናት የፀሎት ጊዜውን እስከመጨረሳው ድረስ አልጨርስም ነበር። የሕይወት ውሃ ምንጭ በአቅራቢያዬ እያለ እኔ የራሴን የማይጠቅሙ የውሃ ጉድጓዶች በመቆፈር በጣም ተጠምጄ ነበር! በዚህ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር ለመሆን እና ቃሉን ለመቀበል ወሰንኩ። ምን ያህል አስገራሚ አስር ቀናት ነበር! በአርማትያው ዮሴፍ መቃብር ላይ ማርያም እየሱስን እንደአየችው ፣ እኔም ኢየሱስን አየሁት ። እሱ ሕያው እንደሆነ እነግራችኋለሁ! ክርስቶስ ፤ በጸሎት ፣ በመታዘዝ እና በእምነት ላይ አዲስ እይታ ሰጥቶኛል። ኃጢአቴን ከተናዘዝኩ በኋላ እንደገና ለጌታ ልቤን ሰጠሁ እና ከእኔ ጋር እንዲኖር ለመንኩት። አሁን ብዙ የምኖርለት ምክንያት አለኝ! "(ቱቶ)

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ - የሐዋርያት ሥራ 1: 8**

"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ፣ በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ። "

**"ኃይልን ትቀበላላችሁ"**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ የሰጠኸንን ሦስተኛውን የመላእክት ተልእኮ ለመፈፀም የሚያስችል አቅም የለኝም እና በራሴ አቅም እንደሌለኝም አውቃለሁ። ይህ በጣም ትልቅ እና በሰብአዊነት ብቻ ለማድረግ የማይቻል ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሀይል ቃልኪዳንህ አመሰግንሀለሁ። በየዕለቱ በመንፈስ ቅዱስ የመጠመቅ አስፈላጊነትን እንዲሁም በአንተ ላይ እምነታቸውን የሚጥሉትን ለማበረታታት በገባኸው ቃል እንደምተማመነን ተገንዝቤያለሁ።

**"እናንተ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"**

ኢየሱስ ሆይ ፣ ስለ ፍቅርህ ፣ ስለእውነትህ እና ስለ የመለወጥ ኃይልህ ምስክር አድርገኸኛልና አመሰግንሃለሁ። በእነዚህ የምድር ታሪክ የመጨረሻ ቀናት ውስጥ ለእኔ ያደረክልኝን በዙሪያዬ ላሉት ለማካፈል እንድችል ድፍረት ስጠኝ። ስለ አንተ ለመመስከር እና ምን ያህል ድንቅ እንደሆንክ ለሌሎች ለመናገር ተጨማሪ እድሎችን ስጠኝ።

**“እስከ ምድር መጨረሻ”**

አባት ሆይ ፣ የተልእኮዬ መስክ ከቤት ጀምሮ ወደ ሰፈሬ ፣ ወደ ማህበረሰቤ ፣ ወደ መንደሬ እና ወደ ከተማዬ እንዲሁም ወደ ዓለም ሁሉ እንደሚሰፋ ተገንዝቤያለሁ። ዛሬ ባለሁበት ተልዕኮውን እንዴት መቀላቀል እንደምችል እና በዓለም ዙሪያ የወንጌልን ሥራ እንዴት እንደምደግፍ አሳየኝ።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

ስለእግዚአብሔር አመራር መጸለይ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች

የ ውዳሴ መዝሙር

የጸሎት ሰአት (63)

ተስፋ ሁንልኝ (134)

ይመራኛል (96)

## 4ኛ. ቀን —የእግዚአብሔር ተልእኮ እና ጸሎት ፣ ክፍል 2

“ለእናንተ በምንፀልይበት ጊዜ የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሄርን ዘውትር እናመሰግናለን ፤ በእየሱስ ክርስቶስ ያላችሁን እምነትና ስለምእመናን ሁሉ ያላችሁን ፍቅር ሰምተናል ፤ የእውነት ቃል የሆነውን ወንጌል በመጀመሪያ ወደ እናንተ በደረሰ ጊዜ በእነርሱ ያለውን ተስደፋ ሰምታችኋል ፤ ስለዚህ እምነታችሁና ተስፋችሁ የተመሰረተው በሰማይ ተዘጋጅቶ በሚቆያችሁ በዚህ ተስፋ ላይ ነው። ”ቆላስይስ 1: 3-6

**ፈጣን እድገት**

የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን በከፍተኛ መጠን አደገች። ከልብ ለመነጨ ጸሎት መልስ ይሆን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይል ወረደ። በአንድ ቀን ፣ በአንድ ቦታ ሦስት ሺህ ሰዎች ተጠመቁ። በሐዋርያት ሥራ 4 ላይ መዝገቡ “ነገር ግን ቃላቸውን ከሰሙት ሰዎች ብዙዎቹ አመኑ ፤ የአመኑትማ ሰዎች ቁጥር ወደ አምስት ሺህ ከፍ አለ”(የሐዋርያት ሥራ 4 4)። ከበአለ ሃምሳ ከጥቂት ጥቂት ወራት በኋላ የአማኞች ቁጥር ሴቶችን እና ሕፃናትን ጨምሮ ፣ በእርግጥ 15,000–20,000 ነበር። በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ቤተክርስያኗ በፍጥነት ማደግ ቀጠለች። የሐዋርያት ሥራ 6 ብዙ ካህናት ወይም የሃይማኖት መሪዎች ለእምነቱ ታዛዥ መሆናቸውን ይገልጻል (ቁጥር 7)። ታሪኩ የፊልጶስን በሰማርያ መስበክ፣ የጳውሎስን በመላው የሜዲትራኒያን ዓለም ሚስዮናዊ ጉዞ፣ የጴጥሮስ ከቆርኔሌዎስ ጋር ቅዱሳት መጻሕፍት ማጥናትን፣ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው የክርስቶስን መልእክት በየቦታው ማካፈላቸውን ይተርካል። የወንጌሉ ተፅዕኖ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌል ከሰማይ በታች ለነበረ ፍጥረት ሁሉ እንደተሰበከ ማወጅ ችሏል። (ቆላስይስ 1 23)።

የጌታችንን መምጣት ስንጠባበቅ የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ተሞክሮ ለዛሬዋ ለቤተክርስቲያን ትምህርት ይሰጣል። ለስኬታቸው ቁልፉ ምን ነበር? በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለችው ቤተክርስቲያን ለምን በፍጥነት አደገች? እስቲ ጥቂት ምክንያቶችን ብቻ እንመልከት። የአዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን አማኞች የሚያደርጉት ሁሉ በፀሎት ላይ የተመረኮዘ ነበር ። በእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ አምነውና እርሱን ተጠግተው ኖረዋል። ያለ ኢየሱስ ኃይል የኢየሱስን ተልዕኮ ለመፈጸም አቅም እንደሌላቸው ተገንዝበው ነበር። ኤለን ኋይት በአጭሩ እንዲህ ትላለች-

"ሥራውን የሚሠራው የእርሱ ሀይል መሆኑን በመገንዘብ ወደ ኢየሱስ ዘወትር መመልከት አለብን። ለጠፉት መዳን በትጋት ስንሠራ ፤ ለማሰብ ፣ ለጸሎት እና የእግዚአብሔር ቃል ለማጥናት ጊዜ መውሰድ አለብን። በብዙ ጸሎት የተከናወነ ፣ በክርስቶስ ክብር የተቀደሰ ሥራ ብቻ ፣ በመጨረሻ በጎ ውጤት ያመጣል።" (የዘመናት ምኞት 362)

**የእግዚአብሔር ተልእኮ - የእግዚአብሔር መንገድ**

ይህንን መመሪያ በጥንቃቄ ያስተውሉ። በእኛ በኩል ሥራውን የሚያከናውነው የክርስቶስ ኃይል ነው ፤ የእኛ ጥበብ፣ አእምሯችን፣ የእኛ ጠባይ ወይም ዕውቀታችን አይደለም። ነፍሳትን የማዳን ጥበብ የሚመጣው ከኢየሱስ ነው። ሕይወትን የመለወጥ ኃይል የክርስቶስ እና የክርስቶስ ብቻ ነው። በመጨረሻም ፣ በብዙ ጸሎት የተከናወነና በክርስቶስ ክብር የተቀደሰ ሥራ ብቻ በመጨረሻ በጎ ውጤት ያመጣል ። የእግዚአብሔር ተልዕኮ በእግዚአብሔር መንገድ መፈጸም አለበት።

በእግዚአብሔር መንግሥት ለማየት የምትፈልገው ሰው አለ? ኢየሱስ የሚያስፈልገው ጓደኛ ወይም የሥራ ባልደረባ አለህ? አማኝ የነበረ አሁን ግን ወደኋላ የቀረ ሰው አለ? ግልጽ በሆነ ወረቀት ላይ ስማቸውን ጻፍ እና ያንን ጽሁፍ በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ በ 1 ዮሐንስ 5: 14-17 ላይ አስቀምጥ። ለምትወዳቸው ሰዎች በእያንዳንዱ ቀን የእግዚአብሔርን ቃልኪዳን አውጅ። አሁን ፣ እኛ እንድንመሰክርላቸው የምንፈልጋቸውን ሰዎች ወደ አእምሯችን እንዲያመጣልን ጌታን እየጠየቅን ጥቂት ጊዜዎችን እናሳልፍ ፣ ከዚያም አብረን እንጸልይላቸው።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ-ቆላስይስ 1: 3-6**

“ለእናንተ በምንፀልይበት ጊዜ የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሄርን ዘውትር እናመሰግናለን ፤ በእየሱስ ክርስቶስ ያላችሁን እምነትና ስለምእመናን ሁሉ ያላችሁን ፍቅር ሰምተናል ፤ የእውነት ቃል የሆነውን ወንጌል በመጀመሪያ ወደ እናንተ በደረሰ ጊዜ በእነርሱ ያለውን ተስደፋ ሰምታችኋል ፤ ስለዚህ እምነታችሁና ተስፋችሁ የተመሰረተው በሰማይ ተዘጋጅቶ በሚቆያችሁ በዚህ ተስፋ ላይ ነው። ”

**“ሁልጊዜ መጸለይ”**

ጌታ ሆይ ፣ እየጸለይን ጊዜ እዳላሳለፍን እንናዘዛለን። ስለዚህ ብዙ ጊዜ እንደምናደርገው ሁሉ በራሳችን ጥበብ እና በእራሳችን እቅዶች ላይ እንመካለን። እናም ተልዕኮህን ለመፈፀም፣ የአንተን መመሪያ በበቂ ሁኔታ አልፈለግንም። እባክህ ይቅር በለን። ስኬታማ ለመሆን ፤ በሰው ሀሳቦች እና ዕቅዶች ላይ ሳይሆን በአንተ የምንታመንን ቤተክርስቲያንና የጸሎት ቤተክርስቲያን እንድንሆን እርዳን። የፀሎት ሕይወታችንን ለውጥ ፤ መነቃቃትን ወደ እኛ አምጣ።

**“በክርስቶስ ያላችሁ እምነት”**

ጌታ ሆይ ፣ በብዙ ጸሎት እና በክርስቶስ ሃይል የተሰራ ስራ ፣ በመጨረሻ በጎ ውጤት እንደሚያመጣ አውቀናል። በሁሉም የቤተክርስቲያናችን ተልዕኮ ጥረቶች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በግል ሕይወታችን እና በቤተሰቦቻችን ውስጥም ፤ ከልብ ለሆነ እና ለጠንካራ ጸሎት ቅድሚያ እንድንሰጥ እርዳን። ለእኛ የገባኸውን ቃል ለመፈጸም ባለህ ችሎታ ላይ ያለንን እምነት ጨምርልን።

**“ፍቅር ለቅዱሳን ሁሉ”**

የፍቅር አምላክ ፣ በፍቅርህ ውስጥ ለማደግ በሚያስችል ዘላለማዊ አቅም ፈጥረኸናል። እኛ ደግሞ በዙሪያችን ያሉትን ለመውደድ እንድንችል ፍቅርህን በልባችን ውስጥ ስላፈሰስክ እናመሰግንሀለን።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ለአለም አቀፍ ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

**ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች**

የ ውዳሴ መዝሙር

የጸሎት ሰአት (63)

ስመለከት ያን ድንቅ መስቀል (179)

ህይቴን ውሰድና (117)

## 5ኛ ቀን - ታዛዥ የአኗኗር ዘይቤ እና ጸሎት

“ማንኛውንም ነገር እንደ እርሱ ፈቃድ ብንለምን እንደሚሰማን እንተማመናለን ፤ የምለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን ከእርሱ የምንለምነውን ሁሉ አሁኑኑ እንደምቀበል እናውቃለን።” 1 ዮሐንስ 5:14-15

### እኛ አቅም የለንም ፣ እርሱ ግን ሁሉን ቻይ ነው

የሦስቱ መላእክት መልእክቶች ወደ መታዘዝ ሕይወት ይጠሩናል። የመጀመሪያው መልአክ መልእክት “የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት” ይላል (ራእይ 14 7)። አዲስ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው የፍርሃት ቃል አክብሮት ወይም ክብር ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ለእግዚአብሔር የመታመን መገለጫው ፣ ለፈቃዱ ለመታዘዝ የሚኖረን የአእምሮ መነሳሳት ነው። ጠቢቡ ሰው ሲናገር እንዲህ ይላል - "እነሆ ሁሉ ነገር ተነግሮአል ፤ የሁሉ ነገር መደምደሚያ ይህ ነው ፤ እግዚአብሄርን ፍራ ፣ ትእዛዛቶቹንም ጠብቅ ፤ ይህ የሰው ዋና ተግባሩ ነው ፤ እግዚአብሄር ስውር የሆነውን ነገር ሳይቀር የሰውን ስራ ሁሉ ክፉውንም ደጉንም ወደፍርድ ያመጣዋል። ”(መክብብ 11:13-14)።

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስለመጠበቅ ስናስብ የእኛን ድክመቶች ፣ ውድቀቶቻችንን ፣ እና የምንፈልገውንና በውስጣችን ያለውን ለማድረግ አለመቻላችንን ለማስታወስ በጣም ቀላል ነው። ብዙ ጊዜ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ እንፈልጋለን ነገር ግን እነዚያን ምኞቶች ለመፈጸም ጥንካሬን ማግኘት አንችልም። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል “እኔ የማደርገውን አላውቅም። የምወደውን ነገር ትቼ የምጠላውን ነገር አደርጋለሁ።” (ሮሜ 7 15)። ለዚህ አጣብቂኝ የሐዋርያው መፍትሔ ምን ነበር? በምዕራፉ መጨረሻ ላይ “ከዚህ ሟች ሰውነት ማን ያድነኛል?” የሚለውን ጥያቄ ይጠይቃል። እናም በዚህ አዎንታዊ የማረጋገጫ ቃል እንዲህ ይላል “በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሚያድነኝ ለእግዚአብሄር ምስጋና ይሁን!” (ሮሜ 7 24፣25)። ደጋግሞ ለመውደቅ ፣ ለመጸጸት እና መልሰ ለመውደቅ የሚሆን መፍትሄ አለ። ጳውሎስ መፍትሄው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላል። እኛ ደካሞች ነን ፣ እርሱ ግን ብርቱ ነው። እኛ ደካሞች ነን ፣ እርሱ ግን ሁሉን ቻይ ነው። እኛ አቅም የለንም ፣ ግን እርሱ ሁሉን ቻይ ነው። ኤለን ኋይት በ1897 በጻፈችው ጽሑፍ ውስጥ በሚያምር ሁኔታ እንዲህ ስትል ገልፃለች-

“የድል ተስፋችን የሰይጣንን ጥቃቶች ያለማቋረጥ መቃወም ብቻ መሆኑን የክርስቶስ ምሳሌ ያሳየናል። ከፈተና ጋር በገጠመ ጊዜ የነፍሳት ጠላት የሆነውን ያሸነፈው ኢየሱስ የሰው ዘር የሚገጥመውን ፈተና ያስተውላል። በእነርሱም ፋንታ አሸንፏል። የሰይጣንን ፈተናዎች ለመቃወም በምናደርገው ጥረት ፤ ድክመታችንን ከኃይሉ ፣ ከንቱነታችንን ከብቃቱ ጋር አንድ ለማድረግ እንድንችል ድል ያደረገው ኢየሱስ ለኛም ያንን የድል ዕድል ሰጥቶናል። በከባድ ፈተናዎች ውስጥ በጸናው ኃይሉ ተደግፈን ፣ ሁሉን ቻይ በሆነው ስሙ ልንቃወምና እርሱ እንዳሸነፈው እኛም ልናሸንፈው እንችላለን” *Signs of the Times,* May 27, 1897

**ድሉን ማወጅ**

በድካማችን ላይ ሳይሆን ፣ በክርስቶስ ኃይል ላይ ከተደገፍን በክርስትና ህይወት አሸናፊዎች እንሆናለን። ወደ ጸሎት ስንገባ ፣ በ 1 ዮሐንስ 5: 14፣15 ላይ የተፃፈውን የተስፋውን ቃል እንጠይቅ "ማንኛውንም ነገር እንደ እርሱ ፈቃድ ብንለምን እንደሚሰማን እንተማመናለን ፤ የምለምነውን ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን ከእርሱ የምንለምነውን ሁሉ አሁኑኑ እንደምቀበል እናውቃለን!" ተስፋ በእምነት ስንጠይቅ ፣ ኢየሱስ አስደናቂ ነገሮችን ያደርጋል፤ በተጨማሪም ዳግም ምጻቱን ስንጠባበቅ ሳለ እግዚአብሔርን የመሰለ ሕይወት እንድንኖር ያበረታናል።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ - መክብብ 12:13-14**

"እነሆ ሁሉ ነገር ተነግሮአል ፤ የሁሉ ነገር መደምደሚያ ይህ ነው ፤ እግዚአብሄርን ፍራ ፣ ትእዛዞቹንም ጠብቅ ፤ ይህ የሰው ዋና ተግባሩ ነው ፤ እግዚአብሄር ስውር የሆነውን ነገር ሳይቀር የሰውን ስራ ሁሉ ክፉውንም ደጉንም ወደፍርድ ያመጣዋል።

**"እግዚአብሔርን ፍሩ"**

ጌታ ሆይ ፣ አንተ ፈጣሪ አምላክ ፣ ሁሉን ቻይ ፣ ሁሉን አዋቂ እንደሆንክ እንገነዘባለን። አንተ ከተገደበው የሰው ልጅ ግንዛቤ በላይ ነህ ፣ ለእኛ ቅርብ ከሆኑና ከምንወዳቸው ሰዎች ይልቅ አንተ ለእኛ ቅርብ ነህ። በግርማዊነትህ እንፈራሀለን ፣ አንተን እናመልካለን ፣ በሕይወታችን አንተን ለማክበር እንፈልጋለን።

**“ትእዛዙን ጠብቁ”**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ ትዕዛዛትህን ለመጠበቅ ፣ ከፈቃድህ ጋር ለመስማማት የሚያስችለን ነገር በውስጣችን የለም። ሊረዳን የሚችለው ኢየሱስ ብቻ ነው። ታማኝ ለመሆን ፣ ፈቃድህን ለማድረግ እንፈልጋለን ፣ ግን ብዙ ጊዜ አልተሳካልንም። ኢየሱስ በሕይወታችን ውስጥ ድልን ለማምጣት ኃይል ስላለው አናመሰግንሃለን። እኛ ወደ እርሱ እንመለከታለን ፤ እራሳችንን ለታመኑት እጆችህ አሳልፈን እንሰጣለን። ኢየሱስ ሆይ ፣ በእኛ ውስጥ እንድትኖር እንለምንሃለን።

**የተሰወረውን ክፉም ሆነ ደግ ነገር**

አባት ሆይ ፣ ከአንተ የተሰወረ ነገር እንደሌለ ተረድቻለሁ። ልቤን ታውቃለህ ፣ ውጣ ውረዶቼን ታውቃለህ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ ስለሚሆነው ነገር ሁሉ አንተ ሙሉ በሙሉ ታውቃለህ። ፣ ምንም ስሜት ቢሰማኝ እንኳን አንተ ለኔ ያለህ ሐሳብ በፍቅር እና በጸጋ የተሞላ ስለሆነ አመሰግንሃለሁ፤ ከእየሱስ ጋር እስከኖርኩ ድረስ ፍርድን መፍራት የለብኝም።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ስለ አለም አቀፍ ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

**ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች**

የ ውዳሴ መዝሙር

ሐይል አለው በደሙ

ካንተ ጋር (162)

ይመራኛል

## 6ኛ ቀን — በፍርዱ ሰዓት የሚኖረን ድፍረትና ጸሎት

"በሰማይ ባለው መንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሄር ይመስገን። ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ አለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን። እግዚአብሄር በጎ ፈቃዱ ሆኖ በእየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ልጆቹ እድንሆን አስቀድሞ በፍቅሩ መረጠን።" ኤፌሶን 1: 3-5

### የፍርዱ ሰዓት ደርሷል

የዮሐንስ ራእይ የመጀመሪያው መልአክ "የፍርዱ ሰዓት ደርሷል" (ራእይ 14 7) የሚለውን መልእክት ያስተላፋል። በዘላለማዊው ነበልባ ነጸብራቅ እይታ የሰማይ መለኮታዊ ፍርድ እውነታ ፤ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ የሆነ ግንኙነትን እንድንሻ ይመራናል። በጥንቷ እስራኤል በስርየት ቀን የሚካሄደው ስርአት ፣ በሰማይ መቅደስ ውስጥ ላለው ፍርድ ፤ እንደማሳያ ነበር። በብሉይ ኪዳን የቤተ መቅደስ ሥርዓት ውስጥ በሥርየት ቀን ፣ እስራኤል ሁሉ በመቅደሱ ዙሪያ ተሰብስበው ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ እና የእግዚአብሔርን ይቅርታ ይጠየቁ ነበር። ዘሌዋውያን 23: 29 በዚያን እለት በንስሃ ራሱን የማያዋርድ ሰው ሁሉ ተለይቶ ይጥፋ" በማለት አጥብቆ ይናገራል። ነፍስን ማጎሳቆል ማለት እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወትን ለመኖር የሚያስችል ኃይልን ከእርሱ በመጠየቅ በንስሐ እና በመናዘዝ እግዚአብሔርን መፈለግ ነበር።

በሰማይ የመጨረሻ ፍርድ ውስጥ የእግዚአብሔር ክብር እና ዝና አደጋ ላይ ነው። ስለ ባሕሪው የሚጠይቁ ጥያቄዎች ከአጽናፈ ዓለም በፊት ተነሱ። እግዚአብሔር ፍትሐዊ ነውን? ትእዛዙ ለመጠበቅ የማይቻል ነውን? እሱ አፍቃሪም እና ፍትሃዊም ነውን? በፍርድ ጊዜ እግዚአብሔር ሁሉንም የሰው ዘር ለማዳን የተቻለውን ሁሉ እንዳደረገ ይገልጣል። ከዚህ በላይ ምን ያድርግ? የእርሱ ጸጋ ለሁሉም ይበቃል። ከሁለቱም የኃጢአት ቅጣት እና ኃይል የሚያድነን ጸጋ ነው። ያለፈውን ይቅር ብሎ የአሁኑን ኃይል የሚሰጥ ጸጋ ነው።

የፍርድ ሰዓት መልእክት አጣዳፊነት ከክርስቶስ ጋር ወደሚነረን ጥልቅ ግንኙነት ይመራናል። ስሙን ለማክበር እና እውቅናውን የማያበላሸውን ነገር ለማድረግ እንናፍቃለን። ክርስቶስ ደጋፊያችን ፣ የፍርድ ጠበቃችን እና ፈራጃችን ስለሆነ ፍርዱን መፍራት የለብንም (ዮሐንስ 5 ፥ 22)። በክርስቶስ እኛ የሰማይ ንጉሣዊ ቤተሰብ አካል ፣ የአጽናፈ ዓለሙ ንጉሥ ወንዶች ልጆች እና ሴቶች ነን። ነቢዩ ዳንኤል በሰማያዊው መቅደስ ውስጥ፤ ኢየሱስ በሰማያዊው የመጨረሻ ፍርድ በአብ ፊት ሲቀርብ ይናገራል። በአስር ሺዎች

የሚቆጠሩ የሰማይ ፍጥረታት በዚህ የፍርድ ቤት ትዕይንት ውስጥ ይኖራሉ። በመልካም እና በክፉ መካከል ያለው ታላቅ ውዝግብ በቅርቡ ያበቃል። የእግዚአብሔር ስም ፣ ባህሪው ፣ በአጽናፈ ዓለም ፊት ከፍ ከፍ ይላል (ዳንኤል 7 9-14)። እርሱ መሐሪ እና ጻድቅ እንደሆነ ፣ የሰማይንም በጣም ውድ ስጦታ በኢየሱስ ውስጥ እንደ ሰጠ ይታያል።

"በሰማይ ባለው መንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሄር ይመስገን። ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ አለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን። እግዚአብሄር በጎ ፈቃዱ ሆኖ በእየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ልጆቹ እድንሆን አስቀድሞ በፍቅሩ መረጠን። ” (ኤፌሶን 1 3-6)።

ዛሬ በጸሎታችን ጊዜ የራሳችንን ልብ እንመርምር እና እግዚአብሔር ከፈቃዱ ጋር የማይስማማ ማንኛውንም ነገር እንዲገልጥ እንለምነው። ከእነዚያ ጥልቅ እና የተደበቁ ኃጢአቶች እንዲያነጻን እንለምነው ከዚያም ስለጸጋው ፣ ስለይቅርታው እና ለማሸነፍ ስላለው ኃይል እናመሰግነዋለን። ከሁሉም በላይ ስለ ኢየሱስ እናመስግነው።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ - ራእይ 14: 7**

"የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ስጡት።"

"እግዚአብሔርን ፍሩ"

አምላኬ ሆይ አንተን እናመልካለን። ክብርና ምስጋና ሁሉ ይገባሃል። አንተ ፣ የሰማይ ግርማ ፣ ፈጣሪ አምላክ ፣ አንተ ዘላለማዊ - እኛ በአንተ እንደነቃን። አንተን የሚይዝ ምንም ነገር የለም።

**“ለእርሱ ክብር ስጡ”**

እግዚአብሔር ፣ የፍቅር ባሕሪህን በእኔ በኩል ለመግለጥ እንደምትፈልግ ማሰቡ ድንቅ ነው። እባክህ በመንፈስ ቅዱስህ ሞልተኸህ የሚገባህን ክብር እንዲታይ አምጣ። በእኔ እና በእኔ ኑር እና በኃጢአት ላይ ድልን ይስጠኝ። ከፈቃድህ ጋር ተስማምቼ እንድኖር ኃይል ስጠኝ።

**“የፍርዱ ሰዓት ደረሶአል”**

ኢየሱስ ፣ ለፍርዱ እመሰግነዋለን። ፍርዱ ለእኛ ስለ ሆነ እና ለዚህ ጽንፈ ዓለም ፍትህ ስለሚመልስ እናመሰግነዋለን። አንተ ጠበቃችን እና ሊቀ ካህናችን ስለሆንክ ፣ ራሳችንን ከፍ አድርገን በደስታ አመስጋኝነት ለመቆም የሚያስፈልገንን የጽድቅ ማረጋገጫ  ስለሰጠን እናመሰግናለን። እኛ የምንኖርበትን ጊዜ አጣዳፊነት አስታውሰን ብዙ ሰዎች በአንተ ውስጥ ዘላለማዊ ቤዛቸውን ለማግኘት እንዲችሉ የተቻለንን ያህል እንድንጠቁም እርዳን።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ -  ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ለአለም አቀፍ ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

**ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች**

የ ውዳሴ መዝሙር

በጌታዬ በክርስቶስ ቃል ላይ ቆሜ

ዳንኩኝ

ወደ ጽዮን እንጓዝ

ሰላም ነው በልቤ

## 7ኛ ቀን - የሦስቱ መላእክት መልእክቶች ፣ ሰንበት እና ጸሎት

"ለእነርሱ በቤተ መቅደሴ እና በግቢዬ ከሴቶችና ከወንዶች ልጆች የተሻለ መታሰቢያ እንዲኖራቸው አደርለጋሁ። ከባእድ ሀገር መጥተው ወደ እግዚአብሄር በመጠጋት እርሱን የሚወዱትንና የሚያገለግሉ ኪዳኑን የሚጠብቁትን ባእዳንን እግዚአብሄር እንዲህ ይላቸዋል- እነርሱን ወደተቀደሰው ተራራዬ አምጥቼ በጸሎት ቤቴም ደስ እንዲላቸው አደርጋለሁ ፤ በመሰዊያዬ ላይ የሚያቀርቡትን የሚቃጠልና ሌሎችን መስዋእቶች ሁሉ እቀበላለሁ ፤ ይህንንም የማደርገው ቤቴ የህዝቦች ሁሉ ጸሎት ቤት ተብሎ ስለሚጠራ ነው።"-ኢሳይያስ 56: 5-7

### ለዓላማ የተፈጠረ

የሦስቱ መላእክት መልእክቶች ፈጣሪያችንን ለማምለክ የቀረበ ጥሪ ነው። እኛ በዝግመተ ለውጥ አልተፈጠርንም። በድንገትም አልመጣንም። እግዚአብሔር ፈጥሮናል ፣ ሕይወት ከኢየሱስ የመጣ ውድ ስጦታ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ "ጌታችንና አምላካችን ሆይ ፣ ሁሉን ነገር ስለፈጠርክ ሁሉም ነገር የተፈጠረውና የሚኖረው በአንተ ፈቃድ ስለሆነ ገናናነት ፣ ክብና ሃይልም ለአንተ ይገባል። "(ራእይ 4 11)። እኛ በእግዚአብሔር ፈቃድ መኖራችንን ማወቅ የሚያስደንቅ ሐሳብ ነው። ሰንበት የተፈጠረው ለዓላማ እንደሆነ ያስታውሰናል። ወደ ኤደን ወደ ገነት ቤታችን ይመልሰናል እናም ለሕይወታችን መልካም ነገር ብቻ የሚፈልገውን አፍቃሪ ፈጣሪያችንን ያስታውሰናል። በመከራ ፣ በበሽታ እና በህመም ዓለም ውስጥ የፍጥረት አምላክ "ከቶ አይጥልህም ፣ ፈጽሞም አይተውህም" (ዕብራውያን 13 ፡ 5) ሲል ቃል ገብቷል። ስለሕይወት ስጦታ እግዚአብሔርን ለማመስገን እና እርሱ ለሕይወታችን ያለውን ልዩ ዕቅዶች ለማወቅ ይህ እውነት ብቻ በጉልበታችን ለመንበርከክ ሊመራን ይገባል።

### ሰንበት - የለጸሎት ፣ ለምስጋና እና ለአዋጅ የሚቀርብ ጥሪ

ሰንበት ደግሞ የመዳንን ስጦታ ያስታውሰናል። እኛ በሰንበት ስናርፍ ፣ በእኛ ፋንታ በክርስቶስ በተጠናቀቀው ሥራ ነው የምናርፈው (ዕብራውያን 4 ፡ 9-10)። በቸርነቱ እናርፋለን። ሰንበት ለእስራኤል ሕዝብ የተሰጠ የሕጋዊነት መስፈርት አይደለም። ቤዛችን በክርስቶስ ላይ ብቻ እና ሙሉ በሙሉ እንድንጠጋው የሚመራን ለሰው ዘር ሁሉ የተሰጠ በጸጋ የተሞላ ቀን ነው(ኢሳይያስ 56: 6,7)። ኢየሱስ የፍጥረት ሳምንቱን እንዲህ በማለት አበቃው ፣ "ሰማያትና ምድር ፣ ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ። በሰባተኛውም ቀን እግዚአብሔር

የሠራውን ሥራ ፈጸመ ፣ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ዐረፈ "(ዘፍ 2 1፣2)። በመስቀሉም ላይ "ተፈጸመ" በሚለው ቃል ሥራውን አበቃ። መጀመሪያ ላይ ከክርስቶስ የመፍጠር ሥራ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረንም። እሱ ሥራውን ጀመረ ፣ እናም እሱ አበቃ። በተመሳሳይ ፣ በመስቀል ላይ ከክርስቶስ የማዳን ሥራ ጋር ምንም ግንኙነት አልነበረንም። የመዳንን ሥራ ጀመረ ፣ እናም ጨርሶ አበቃ። ለድነታችን እንዲህ ያለ ከፍተኛ ዋጋ በከፈለው በክርስቶስ ፍቅር እንድንደሰት ፣ በእርሱ እንክብካቤ እንድናርፍ እና እንድናከብረው ያስታውሰናል። ሰንበት ለጸሎት ፣ ለምስጋናና የክርስቶስን በጎነት ለማወጅ የቀረበ ጥሪ ነው።

ሰንበት እንዲሁ ባድማ በሆነ የሀዘን ዓለም ውስጥ ብቻችንን እንዳልሆንን ያስታውሰናል። በዚህ ዓለም መከራ ወቅት ፣ የተፈጥሮ ውበቶች አሁንም ስለ ፈጣሪያችን አምላክነት ይናገራሉ። ሰንበት ወደ ፍጥረት ይመልሰናል ፣ ግን ደግሞ እግዚአብሔር አዲሱን ሰማይን እና አዲሲቱን ምድር ወደ ፊት ይጠቁመናል ፣ እግዚአብሔር ይህንን ዓለም በኤደን እንደገና አስገራሚ አድርጎ ይፈጥራል።

ሰንበት የምስጋና ቀን ነው። እግዚአብሔር ስለፈጠረን እና ለሕይወታችን ዕቅዶች ስላለው አመስጋኞች ነን። ስላዳነን እና እንደዚህ ያለ ወሰን የሌለው ዋጋ ስለከፈለልን እናመሰግናለን። እርሱ ስለ ለእኛ ሲል ተመልሶ ስለሚመጣ እናመሰግናለን ፤ እርሱ አዲስ ሰማይን እና አዲስ ምድርን ይፈጥራል። ስንጸልይ ሰሳለን በምስጋና በተሞሉ ልቦች ሆነን እርሱን እንፈልግ።

የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)

የእግዚአብሔርን ቃል እያነሳን(እየጠቀስን) መጸለይ-ኢሳይያስ 56: 5-7

"ለእነርሱ በቤተ መቅደሴ እና በግቢዬ ከሴቶችና ከወንዶች ልጆች የተሻለ መታሰቢያ እንዲኖራቸው አደርለጋሁ። ከባእድ ሀገር መጥተው ወደ እግዚአብሄር በመጠጋት እርሱን የሚወዱትንና የሚያገለግሉ ኪዳኑን የሚጠብቁትን ባእዳንን እግዚአብሄር እንዲህ ይላቸዋል- እነርሱን ወደተቀደሰው ተራራዬ አምጥቼ በጸሎት ቤቴም ደስ እንዲላቸው አደርጋለሁ ፤ በመሰዊያዬ ላይ የሚያቀርቡትን የሚቃጠልና ሌሎችን መስዋእቶች ሁሉ እቀበላለሁ ፤ ይህንንም የማደርገው ቤቴ የህዝቦች ሁሉ ጸሎት ቤት ተብሎ ስለሚጠራ ነው።”›

**“ለእነሱም እንኳን” (ለባእዳኑም ቢሆን)**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ ሁላችንንም ፈጥረኸናል። ወደ ሕልውናህ እድንመጣ ፈቅደህናል እና ከእኛ ጋር ዘላለማዊ ኅብረት ትፈልጋለህ። አዎ ፣ የሰውን ዘር ሁሉ መዳን ትናፍቃለህ። እያንዳንዱ ብሔር ፣ ነገድ እና ሕዝብ እንዲድን ትፈልጋለህ። እናመሰግንሃለን! ይህንን እውነታ ስለሚያስታውሰን ሳምንታዊው ሰንበትም እናመሰግናለን።

**“ሰንበትን የማያረክስ ሁሉ”**

ጌታ ሆይ ፣ ብዙ ጊዜ ሰንበትን ጥሰናል ወይም አልቀደስነውም። እባክህ ይቅር በለን። እባክህን የሰንበትን ሰዓቶች እንድንጠብቅ እና በተለይም በሰንበት ወቅት አንተን እንድናምንህ እና እንድናከብርህ እርዳን። በሰንበት በሳምንቱ ውስጥ ስለ ታማኝነትህ እንድናከብርህ እና እንድንመሰክር በየቀኑ ፈቃድህን ለማወቅ እና ለማድረግ ዓይኖቻችንን እና ጆሮዎቻችንን ክፈት።

**“ኪዳኔን ያከብራል”**

ኢየሱስ ሆይ፣ ሰንበት ፈጣሪያችን ለማስታወስ ምልክት እና ዕድል ብቻ ሳይሆን የመዳን ምልክትም ስለሆነ አናመሰግንሃለን። የቃል ኪዳኑን አጥብቀን ስንይዘው በሚሸፍነው እና በሚሞላው የፅድቅህ ማረጋገጫ ውስጥ ማረፍ ስለቻልን እናመሰግንሃለን። የእኛ ሰንበት ማክበር አንተ ለእኛ ላለህ ታማኝነት የዕለት ተዕለት ተሞክሮ ነፀብራቅ ይሁነን።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ለዓለም አቀፍቨቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች

የውዳሴ መዝሙሮች

ሰንበትን አንርሳ

የሰንበት ቀን ቅዱስ ቀን ናት

የሱስ የልቤ ወዳጅ ወደ አንተ አስጠጋኝ

ወደ ጽዮን እንጓዝ

## 8ኛ ቀን - የባቢሎን ውድቀት እና ጸሎት

“ከዚህ በኋላ ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ ፣ ምድርም በክብሩ በራች። ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች ፣ ወደቀች ፣ የአጋንንት መኖሪያ ሆነች፣ የርኩሳን መናፍስትማደሪያ ሆነች ፣ የሚያጸይፉና የሚያስጠሉ ወፎች ሁሉ ዋሻ ሆነች! ”በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ራእይ 18: 1-2

### የሁለተኛው መልአክ መልእክት

የዮሐንስ ራእይ 14 ላይ ያሉት የሦስቱ መላእክት መልእክቶች የእግዚአብሔርን ሕዝብ በተለየ መልኩ ለኢየሱስ መምጣት ለማዘጋጀት የተሰጡ ናቸው። እነሱ የእግዚአብሔርን እቅዶች የሚገልጡና የዲያቢሎስን እቅዶች የሚያጋልጡ። የሁለተኛው መልአክ መልእክት ይህን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል - “የሚያሰክረውን የዝሙቷን ወይን ጠጅ ለህዝቦች ሁሉ ያጠጣች ያቺ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች ፣ ወደቀች” (ራእይ 14 8)። የጥንቷ ባቢሎን በትእዛዙ ላይ በማመፅ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ተዋጋች ሁሉ መንፈሳዊዋ ባቢሎን በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ትቆማለች። በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ለማታለል የሐሰት ትምህርቶቿን ጽዋ ታስተላልፋለች። ኤለን ኋይት ባቢሎንን እንዲህ በማለት ገልጻለች - “ባቢሎን የተከሰሰችበት ታላቅ ኃጢአት‘ አሕዛብን ሁሉ ከዝሙትዋ ቁጣ ወይን ጠጅ ማጠጣቷ ነው ። ይህ የወይን ጽዋ ከምድር ታላላቅ ሰዎች ጋር በሕገ -ወጥ ግንኙነትዋ ምክንያት የተቀበለችውን የሃሰት ትምህርት ይወክላል። ከዓለም ጋር ያላት ወዳጅነት እምነቷን ያበላሸዋል ፣ በእሷ በኩል የመጽሀፍ ቅዱስን ግልፅ መግለጫዎች የሚቃወሙ ትምህርቶችን በማስተማር በዓለም ላይ የተበላሸ ተጽዕኖ ታሳድራለች (GC, 388)። ዝሙት ሕገ ወጥ ሕብረት ነው። መንፈሳዊ ባቢሎን ከእውነተኛ አፍቃሪዋ ከኢየሱስ ተለይታ ከመንግስት ወይም ከፖለቲካ ኃይሎች ጋር ትዋሃዳለች።

በራዕይ 17 ላይ እንደተገለጸው ይህ የቤተክርስቲያን እና የመንግሥት ህብረት ወደ አውሬው ምልክት ተፈጻሚነት ይመራል። ባቢሎን መጽሀፍ ቅዱስን የሚያዛባ እና በሰው ትምህርት ውስጥ ያተኮረ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው። የሁለተኛው መልአክ መልእክት ፣ ከራዕይ 17 እና ከራእይ 18 ትንቢቶች ጋር ተደምሮ ፣ በዚህ ምድር ላይ የሚመጣውን እጅግ አስገራሚ እና አስደንጋጭ ነገር ያሳያል። ከሃዲ ኃይማኖታዊ ኃይሎች በዓለም አቀፍ ቀውስ እና ጥፋት ወቅት አንድነትን ለማምጣት ከፖለቲካ እና ኢኮኖሚያዊ ኃይሎች ጋር አንድ ይሆናሉ።

የሁለተኛው መልአክ መልእክት ቢያንስ በሦስት መንገዶች ለጸሎት አስቸኳይ ጥሪን ያሰማል። በመጀመሪያ፣ ለክርስቶስ እና ለቃሉ ታማኝ እንድንሆን ይጠራናል። ከግል ሕይወታችን ጋር መጣጣም በመጨረሻው ዘመን እኛን ከባቢሎን ጋር ለመዋሃድ እና ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር ወደማዋጋት ይመራናል።

ሁለተኛ ፣ ይህ መልእክት የፍርድ ፈተናውን መቋቋም ወደሚችል እምነት ይጠራናል። የእግዚአብሔር ነቢይ እኛን አጥብቆ ይለምነናል ፣ "በቶሎ የማያልቅ አውሎ ነፋስ ይመጣል። እሱን ለመጋፈጥ ተዘጋጅተናል? እኛ ፣ የመጨረሻዎቹ ቀናት አደጋዎች በቅርቡ ይመጡብናል ማለት የለብንም። ቀድሞውኑ መጥተዋል። አሁን የሥጋ ምኞትን ፣ የምግብ ፍላጎትን እና ስሜትን ለመቁረጥ የጌታ ሰይፍ ያስፈልገናል። ለላላ አስተሳሰብ የተሰጡ አዕምሮዎች መለወጥ ያስፈልጋቸዋል። . . .ሀሳቦቹ በእግዚአብሔር ላይ ያተኮሩ መሆን አለባቸው "(With God at Dawn, p. 113)።

ሦስተኛ ፣ ይህ መልእክት ጓደኞቻችንን ከኢየሱስ ጋር ወደ ጥልቅ ግንኙነት እና በመጨረሻው ሰዓት ለራዕይ እውነታዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንድንጋብዝ ይጋብዘናል። ለመጸለይ ተንበርክከን ፣ ስለ እነዚህ የተወሰኑ ነገሮች እንጸልይ -

1. የእግዚአብሔርን ቃል የበለጠ ለመረዳት ፣ ለኢየሱስ የበለጠ ፍቅር እንዲኖረን እና ያለመደራደር መንፈስ እንዲሰጠን
2. ከባዱን ፈተና መቋቋም የሚያስችል እምነት እንዲሰጠን።
3. በዙሪያችን ላሉት ለመመሥከር ድፍረት እንዲሰጠን።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ - ራእይ 14: 8**

“የሚያሰክረውን የዝሙቷን ወይን ጠጅ ለህዝቦች ሁሉ ያጠጣች ያቺ ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች ፣ ወደቀች” (ራእይ 14 8)

**“ባቢሎን ወደቀች”**

የዘላለም አባት ፣ ከቅዱስ ቃልህ ባሻገር ፣ በዚህ ዓለም ውስጥ ለሕይወት ጽኑ እና የሚታመን አስተማማኝ መሠረት የሆነ ምንም ነገር የለም። በጸጋህ ፣ በመንፈስህ ፣ በቃልህ ላይ ብቻ ሕይወታችንን እንድንገነባ እርዳን።

**“አሕዛብን ሁሉ አሰከረች”**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተን የማወቅ እና በቃልህ የእውነትን ግንዛቤ የማግኘት ልዩ መብት አለን። እኛም ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የእኛን ሃላፊነት እንገነዘባለን። ዛሬ በሐሰት ሃይማኖቶች ለተያዙ በቢሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች እንጸልያለን። ስለማንነትህ እና ምን ያህል እንደምትወዳቸው እና ወደ እውነት ሙላት እንዲገቡ እንደምትፈልግ እንድናሳያቸው እርዳን።

**“የዝሙትዋ ቁጣ ወይን”**

ኢየሱስ ሆይ፣ አንዳንድ ጊዜ በሰይጣን ብዙ ማባበያዎች እና ፈተናዎች እንደተዘናጋን አንደብቅም። አንዳንድ ጊዜ እኛ ወደ አንተ መመልከታችንን እናቆምና በራሳችን እና ራስ ወዳድነትን በተሞሉ ልምዶች ላይ እናተኩራለን። እባክህ ይቅር በለን። ለሥጋዊ ተፈጥሮአችን ከመሰጠት አድነን ፣ አንተ ብቻ የምትሰጠውን ድል በእኛ ውስጥ አኑር።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

ምስጋና እና ውዳሴ - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

**ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች**

የውዳሴ መዝሙሮች

ይመጣል ተዘጋጅተን እንጠብቅ

የሱስ ሆይ አትለፍብኝ

የክርስቲያን አርበኞች

ወደ የሱስ ተመልከት

## 9ኛ ቀን - የአውሬው ምልክት እና ጸሎት

"ከዚህ በኋላ እንዲህ የሚል የብዙዎች ሰዎችን ድምጽ የሚመስል ድምጽ በሰማይ ሰማሁ፤ ሃሌሉያ! ማዳንና ክብር ሃይልም የአምላካችን ነው! ፍርዱ እውነትና ትክክል ነው፤ ምድርን በአመንዝራነቷ ያረከሰችውን ታላቂቱን አመንዝራ በፍርድ ቀጥቶአታል፤ እርሷን በመቅጣትም የአገልጋዮቹን ደም ተበቅሎአል፤ እንደገናም ሃሌሉያ! ከእርሷ የሚነሳው ጢስ ለዘለአለም እስለ ዘለአለም ወደላይ ይወጣል፤ እያሉ ጮኹ። ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችና አራቱ እንስሶች በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው አምላክ በግንባራቸው ተደፍተው አሜን ሃሌሉያ እያሉ ሰገዱ።"-ራእይ 19 ፡ 1-5

**ከባድ ማስጠንቀቂያ**

ከሦስቱ መላእክት መልእክቶች ሦስተኛው እና የመጨረሻው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ጥብቅ ከሆኑ ማስጠንቀቂያዎች አንዱ ነው። ብዙ ሰዎች ችላ ሊሉት የሚፈልጉት ፣ ነገር ግን ጥልቅ ፍላጎቶቻችንን የሚናገሩ እና ወደ ኢየሱስ እንድንቀርብ የሚያደርጉንን ሕይወት የሚቀይሩ መንፈሳዊ እውነቶችን ይገልጣል። "ሌላ ሶስተኛ መልአክም ከፍ ባለ ድምጽ እንደዚህ እያለ ተከተላቸው ፤ ለአውሬውና ለምስ የሚሰግዱ ምልክቱን ሁሉ በግንባራቸው ወይም በእጃቸው የሚያደርጉ ሁሉ የእግዚአብሄርን የቁጣ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ፤ ይህም የወይን ጠጅ ሳይበረዝ በቁጣው ጽዋ የተቀዳ ነው፤ እንዲሁም በቅዱሳን መላእክት ፊትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያሉ" (ራእይ 14፡ 9-10)።

ይህንን ማስጠንቀቂያ በተመለከተ የመጀመሪያው ሕይወትን የሚለውጠው መርህ በመንግስቱ ውስጥ ከምንም በላይ እኛን ለማዳን ከሚፈልግ አፍቃሪ እግዚአብሔር ልብ የመጣ ነው። መልእክቱ የእግዚአብሔር ሰዎች በሚመጡት ማታለያዎች እንዳይያዙ የሚያስጠነቀቅቅ መለኮታዊ የማስጠንቀቂያ መልእክት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ከአምልኮ ጋር የተያያዘ ነው። መልአኩ "ማንም ለአውሬው ቢሰግድ" ይላል። ይህ በቁጥር 7 ላይ ከመጀመሪያው መልአክ "ፈጣሪን ማምለክ" መልእክት ጋር በቀጥታ ይቃረናል። ታማኝ የክርስቶስ ተከታዮች ፈጣሪን ማምለካቸው ለፍቅሩ ምላሽ እንዲሰጡ ፣ የማዳን ጸጋውን እንዲያምኑ ፣ ለቃሉ እንዲታዘዙ እና ትእዛዛቱን እንዲጠብቁ ያደርጋቸዋል። አውሬውን ማምለክ ግን ሰዎችን ለቃሉ ባለመታዘዝ ከእግዚአብሔር በመለየት የራስን ሕይወት ወደ መኖር ይመራቸዋል። በኢየሱስ ላይ ከማተኮር ይልቅ በራስ ላይ ያተኩራል።

**በውስጣችን ያለው አውሬ**

ይህ የሦስተኛው መልአክ መልእክት የሚናገረው ቤተክርስቲያን እና መንግስት በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን አምልኮን ለማስፈፀም በጳጳሱ ስልጣን ስር ስለሚዋሃዱበት ጊዜ ነው። የሦስቱ መላእክት የመጨረሻ መልእክት ከልብ ለመነጨ እውነተኛ ጸሎት ጥሪ ነው። የክርስቶስ ተቃዋሚ መርህ የሆነው -ከትህትና ይልቅ ኩራት ፣ ለሌሎች መልካምነት ሲባል ራስን መስዋዕት ከማድረግ ይልቅ ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ ፣ መለኮታዊ ከሆኑ የመጽሀፍ ቅዱስ ትምህርቶች ይልቅ በሰው ጥበብ መታመን- በወደቀው ተፈጥሮአችን ውስጥ በጥልቀት ስር ሰዷል። በውስጣችን ላለው የአውሬው መርሆዎች መፍትሄው ምንድነው? አንድ መፍትሔ ብቻ አለ ፣ እርሱም ኢየሱስ ነው - ጸጋው ፣ ኃይሉ እና ፍቅሩ ልባችንን እና ሕይወታችንን ይሞላል። ዛሬ እርሱን ለመከተል ያለን ቁርጠኝነት ዓለም ከሚጎትተን ስበት የበለጠ ካልሆነ ፤ በአውሬው መርሆዎች እንገዛና አንድ ቀን የአውሬውን ምልክት እንቀበላለን። ውስጣችንን በሚገባ እንዲያጠራ መንፈሱን እየጠየቅን የመለኮታዊው ጸጋ ተአምር በልባችን ውስጥ እንዲሠራ በሦስተኛው መልአክ መልእክት ውስጥ ለያውና ለአውሬው ምልክት እንዳንሰግድ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ለክርስቶስ በመዋረድ በጉልበታችን እንድንንበረከክ ሊያደርገን ይገባል። ቤተሰቦቻችን ፣ ጓደኞቻችን እና ጎረቤቶቻችን ለክርስቶስ የማዳን የመጨረሻ ቀን መልእክት ልባቸው ክፍት እንዲሆን ለነሱም ወደ መጸለይ ሊመራን ይገባል። ይህ መልእክት ከክርስቶስ ጋር በዙፋኑ ዙሪያ ለዘላለም የምንደሰትበትን ቀን በጉጉት እንድንጠብቅ ሊያነሳሳን ይገባል (ራእይ 19 1-5)።

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ መጸለይ - ራእይ 14: 9, 10**

"ሌላ ሶስተኛ መልአክም ከፍ ባለ ድምጽ እንደዚህ እያለ ተከተላቸው ፤ ለአውሬውና ለምስ የሚሰግዱ ምልክቱን ሁሉ በግንባራቸው ወይም በእጃቸው የሚያደርጉ ሁሉ የእግዚአብሄርን የቁጣ የወይን ጠጅ ይጠጣሉ፤ ይህም የወይን ጠጅ ሳይበረዝ በቁጣው ጽዋ የተቀዳ ነው፤ እንዲሁም በቅዱሳን መላእክት ፊትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሰቃያሉ"።

**"ማንም ለአውሬውና ለምስሉ ቢሰግድ"**

እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ የምታስብልን አምላክ ነህ ፣ ማንም እንዳይጠፋ ነገር ግን ሁሉም እንዲድን የምትፈልግ አምላ ነህ፤ ብዙ ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ላለው ስብራት የሐሰት ሐይማኖቶችን፣ የተጠማዘዙ ፍልስፍናዎችን እና የዘመናችን ጣዖታትን የጥንካሬያቸው ምንጭና የህይወታቸውን ባዶነት የሚሞላ አድርገው ይመለከታሉ። እነሱን እስከማስጠንቀቅ ድረስ ስለምታስብላቸው እና አምልኮ ወደሚገባው ብቸኛው እውነተኛ አዳኝ ወደ ኢየሱስ የመምራትን ሚና ለኛ ስለሰጠኸን እመሰግንሀለን ።

**"የእግዚአብሔር ቁጣ"**

እግዚአብሔር ፤ ለኃጢአት ፣ ለክፋት እና ለተንኮል ያለህ ቅዱሱ ቁጣህ ታላቅ መጽናናትን ይሰጠናል። አንተ ኃጢአትን ለማጥፋት የወደድክ ስለሆንክ አናመሰግንሀለን ፤ አንድ ቀን በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ፍጹም ፍቅርን፣ ሰላምን እና ስምምነትን እንደገና ስለምትመሰርት እናመሰግንሀለን። ሰዎችን ለማዳን እንጂ ለማውገዝ እንደማትፈልግ በኢየሱስ በግልፅ በኩል ስላሳየኸን እናመሰግንሀለን። ለእያንዳንዱን ሰብዓዊ ፍጡር በክርስቶስ መዳንን ለመቀበል ምርጫ እና ዕድል ስለሰጠኸው እናመሰግናለን። እባክህን እና የከክርስቶስ ተቃዋሚውን ትዕቢት ኩራት ከመከተል አድነን ጠብቀንም። ይልቁንም በጉን በሄደበት ሁሉ እንድንከተለው ምራን።

**"በበጉ ፊት"**

ኢየሱስ ሆይ፣ የአንተ የጸጋ እና የመዳን ስጦታዎች ከፍትህ ያልተለየ እንደሆነ የመጨረሻው ፍርድ በግልፅ የሚያሳየን መሆኑን ማወቃችን ታላቅ መጽናናትን ይሰጠናል። ራሳቸውን ላንተ ያስከቡትን እና አሳልፈው

የሰጡትን ሰዎች ሁሉ ቅጣታቸውን ስለወሰድክ እናመሰግንሀለን። ከኃጢአት ጋር መጣበቅ የመረጡትን ጥፋት መመልከቱ ከባድ ቢሆንም ፣ በሁሉም ግንኙነቶች ውስጥ ፍትሃዊ ፣ ትክክለኛ እና ደግ እንደሆንክ ሁሉም ሰው ይናገራል።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

<u>ምስጋና እና ውዳሴ</u> - ስለበረከቶች እና ስለ ቸርነቱ እግዚአብሔርን አመስግኑ።

<u>መናዘዝ</u> - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለ ይቅርታው አመስግኑት።

<u>የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ</u> - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

<u>ለአለም አቀፍ ቤተክርስቲያናችን</u> - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።

<u>የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች</u> - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።

<u>አዳምጥ መልስ መስጠት-</u> የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት ጊዜ ይውሰዱ።

ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች

*የውዳሴ መዝሙር*

የክርስቲያን አርበኞች ለጦር ስትሄዱ

*ወንድሜ ታማኝ ሁን*

ክርስቲያናት ትጉ ጠብቁ

ነፍሴ ደስ የምትሰኝብህ ጌታ

## 10ኛ ቀን - የእግዚአብሔር ቅሬታዎች እና ጸሎት

"የእግዚአብሄርን ትእዛዝ የሚጠብቁት እየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትእግስታቸው በዚህ ነው።" ራእይ 14:12

### የመጨረሻው ግብ

የሦስቱ መላእክት መልእክቶች አንድ ዋና ዓላማና ትኩረት አላቸው - ለኢየሱስ መምጣት ሕዝብን ማዘጋጀት። ዮሃንስ የእግዚአብሔር መንግሥትን የፍጻሜ ዘመን መልእክት የመረዳትና የመቀበልን የመጨረሻ ውጤት እያብራራ ባለበት ፤ እነዚህ በመለኮት አነሳሽነት የተላኩ መልእክቶች በዮሐንስ ራእይ 14፡12 ላይ ወደ መጨረሻ ያደርሳቸዋል። እነዚህ መልዕክቶች "የእግዚአብሄርን ትእዛዝ የሚጠብቁት እየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትእግስታቸው በዚህ ነው።" የሚባልላቸውን ህዝብ እንደሚፈጥሩ ሐዋርያው ይጠቅሳል። (ራእይ 14 12)።

ትዕግስት የሚለው ቃል በተሻለ ጽናት ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የእግዚአብሔር ሰዎች በእሱ ጸጋ የመጨረሻዎቹን ቀናት ፈተናዎች ይቋቋማሉ ፣ በአሸናፊነትም ይወጣሉ። የአውሬውን ቁጣ ይጋፈጣሉ ፣ ንቃተ ህሊናቸውንም ለአውሬው አይሰጡም። ምንም እንኳን ስለ ክርስቶስ ሲሉ መግዛት ወይም መሸጥ ባይችሉና ስደት ፣ እስራት እና ሞት ራሱ ቢገጥማቸውም ፣ ለጌታ ትዕዛዛት ይታዘዛሉ። ለክርስቶስ ያላቸውን ታማኝነት አሳልፈው እንዲሰጡ መገደድ አይችሉም። እነሱ በመጨረሻው ሰዓት በኃጢአተኛ ፣ ዓመፀኛና ታዛዥ ባልሆነው ዓለም ውስጥ በጸጋ ተሞልተው ፣ ክርስቶስን ከፍ በማድረግ ፣ለእርሱ በመታዘዝ ይኖራሉ።

### የኢየሱስ እምነት

በራእይ 14:12 ላይ ሌላ የሚያስገርም ነገር አለ። እነዚህ የፍጻሜ ዘመን አማኞች በኢየሱስ ማመን ብቻ ሳይሆን የኢየሱስ እምነትም አላቸው። የኢየሱስ እምነት ምንድነው? የኢየሱስ እምነት ፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ እያለ በእግዚአብሄር ላይ ከነበረው እምነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ እምነት ነው። ኢየሱስ የሰው ልጆች ኃጢአት የሆኑትን ጥፋተኝነትን ፣ እፍረትን እና ኩነኔን ተሸክሞ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ፣ በእግዚአብሔር እንደተተወ ተሰማው። ኃጢአት ከመጠን በላይ ግዙፍ ከመሆኑ የተነሳ ኢየሱስ አባቱ እንደተለየው ተሰማው። "አምላኬ ፣ አምላኬ ፣ ለምን ተውከኝ?" በማለት በሥቃይ የጮኸው ለዚህ ነው። (ማቴዎስ 27:46)።

እግዚአብሔር ትቶት ነበርን? በፍፁም! የአባቱ ዓይኖች ሁልጊዜ በመስቀሉ ላይ ነበሩ። ልጁ እየደረሰበት በነበረው ሥቃይ የፍቅር ልቡ ተሰብሯል። ኢየሱስ ማየት በማይችልበት ጊዜም ቢሆን ታመነ። እምነቱ በዙሪያው ካለው ነገር ያለፈ ነበር። ለዚያም ነው የመጨረሻ ቃላቱ "አባት ሆይ ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" (ሉቃስ 23 46) የነበረው።

በዮሐንስ ራእይ ትንቢቶች መሠረት ኢየሱስ ከመመለሱ በፊት ፣ በዙሪያቸው ያለው ሁሉ በእነሱ ላይ የተነሳባቸው በሚመስልበት ጊዜ የእግዚአብሔር ሰዎች እምነት ያስፈልጋቸዋል። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ውስጥ የሚያሳልፋቸው ምንድነው? እሱም "የኢየሱስ እምነት" ነው። ይህንን የኢየሱስን እምነት እንዴት እናሳድጋለን? መጀመሪያ፣ መዳን ስጦታ እንደመሆኑ መጠን ፣ ልክ እንደ መዳን እምነትም እኛ በምንለማመደው ቁጥር የሚያድግ ፤ እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ ያስቀመጠው ስጦታ ነው። (ሮሜ 12 3-8)። አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ሲያጋጥሙን እና የእግዚአብሔርን ተስፋዎች አጥብቀን ስንይዝ ፣ እምነታችን ያድጋል። አእምሮአችንን በእግዚአብሔር ቃል ስንሞላ ፤ እምነታችን ያድጋል (ሮሜ 10 17)። የእምነታችንን እጥረት አውቀን እግዚአብሔር እምነታችንን እንዲጨምር ከልብ ስንጸልይ ፤ እምነታችንያድጋል (ሉቃስ 17 5)።

ዛሬ በጸሎት ጊዜያችን፤ የሕይወትን ፈተናዎች ስንጋፈጥ ጽናትን እንዲሰጠን እግዚአብሔርን እንለምነው። በሁሉም የሕይወታችን አካባቢዎች ለፈቃዱ ለመታዘዝ እንድንችል ብርታቱን እንዲሰጠን እንጸልይ። "የኢየሱስ እምነት" ሕይወታችንን ሞልቶ ለምድር የመጨረሻው ዘመን ቀውስ  እንዲያዘጋጀን በእምነት እንድግ ዘንድ እንዲያስችለን ዘንድ ሰማይን እንጠይቅ። ከዚያ አንድ ቀን ለዘላለም ከኢየሱስ ጋር እንኖራለን!

**የጸሎት ጊዜ (ከ30-45 ደቂቃዎች)**

**የእግዚአብሔርን ቃል እያነሱ  መጸለይ - ራእይ 14:12**

"የእግዚአብሄርን ትእዛዝ የሚጠብቁት እየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትእግስታቸው በዚህ ነው።"

**"የቅዱሳን ትዕግሥት በዚህ አለ"**

ጌታ ሆይ ፣ መመለስህን ለረጅም ጊዜ ጠብቀናል። የአንተ ጊዜ መቼም እንደማይሳሳት እና ለእኛ የሚበጀንን እንደምታውቅ እናውቃለን። መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ሲኖር ፣ ትዕግሥትን እና ጽናትን በውስጣችን ስለሚያፈራ እናመሰግናለን። አሁንም ያለንን ጊዜ አንተን ለማክበር እንዴት በተሻለ መንገድ እንደምንጠቀም

አሳየን። ፈተናዎች እና መከራዎች ሲያጋጥሙን ፣ ጥንካሬን እና መለኮታዊ ትዕግሥትን እንደምትሰጠን በማወቃችን እንጽናናለን።

**“ትእዛዛትን የሚጠብቁ”**

እግዚአብሔር ሆይ የአንተ ፈቃድ ፍቅር ነው። ለአንተ እና ለሌሎች ፍቅር! በእግዚአብሔር ቃል እና በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ እንደተገለጠው ፍቅር! ዓመፀኛ ልቤን ከታላቁ የፍቅር ሕግ ጋር እንዲስማማ አድርገህ ለመለወጥ  ፈቃደኛ በመሆንህ እና በመቻልህ ደስ ይለኛል።

**“የኢየሱስ እምነት”**

እግዚአብሔር ሆይ፣ ኢየሱስ እዚህ ምድር ላይ  በተለይም በመስቀል ላይ ሲሞት ባሳየው እምነት እና ታማኝነት እደነቃለሁ ። በአብ ላይ ያለው እምነት ለእኛ ምሳሌ እንደመሆኑ መጠን የእሱ እምነት በዚያ አያበቃም ፤ ነገር ግን ያንን ተመሳሳይ እምነት ለማዳበር እንዲችሉ እድሎችን ለሚያምኑ ሁሉ ይሰጣል። ኢየሱስ ፣ እባክህን እምነታችንን በየቀኑ አሳድግልን፣ ራሳችንን ላንተ ውድና ታማኝ አዳኛችን እናስረክባለን።

**ቢጸለይባቸው ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው ርእሶች**

- ምስጋና እና ውዳሴ -  ስለበረከቶች እና ስለቸርነቱ እግዚአብሔርንአመስግኑ።
- መናዘዝ - ለግል መናዘዝ ጥቂት ደቂቃዎችን ይውሰዱ ፤ እግዚአብሔርን ስለይቅርታው አመስግኑት።
- የእግዚአብሔርን አመራር መጠየቅ - በአሁኑ ጊዜ ላሉ ፈተናዎች እና ውሳኔዎች ጥበብን እንዲሰጥ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።
- ለአለም አቀፍ ቤተክርስቲያናችን - ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ለሚያስፈልጓት ነገሮች ጸልዩ (ከጥያቄዎች ጋር የተለያዩ ጥቅሶች ይመልከቱ)።
- የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥያቄዎች - ለቤተክርስቲያኗ አባላት ፣ ለቤተሰብ እና ለጎረቤቶቻችሁ ወቅታዊ ፍላጎቶች ጸልዩ።
- አዳምጦ መልስ መስጠት- የእግዚአብሔርን ድምጽ ለማዳመጥ እና በምስጋና ወይም በመዝሙር መልስ ለመስጠት  ጊዜይውሰዱ።

**ቢዘመሩ ብለን ሃሳብ የምንሰጥባቸው መዝሙሮች**

የውዳሴመዝሙር

ግሩም ጸጋው (#65);

ሁላችንም ሰማይ ስንደርስ (#223);

ከበረዶ እነጻለሁ (#43);